# የክቡር ዶክተር ሐዲስ ዓለማየሁ የሕይወት ታሪክ፤ አጭር ማስታወሻ

አስፋው ዳምጤ

በምዕራቡ ዓለም የግለሰብን የሕይወት ታሪክ በጽሑፍ አዘጋጅቶ ለሕዝብ ማቅረብ፥ በጣም የተለመደ የረዥም ጊዜ ባህል ነው። ዝግጅቱም፥ በባለታሪኩ በራሱ ወይም በሌላ ሰው ሊሆን ይችላል።

በኢትዮጵያችን ግን፥ እንኳን በባለታሪኩ በራሱ ይቅርና፥ በሌላ ሰውም ተዘጋጅቶ የሚቀርብበት ልምድ ባዕድ ሆኖ ለረዥም ጊዜ ኑሯል። በመሆኑም፥ ለሀገራቸውና ለወገናቸው ታላላቅ ተግባራት ፈጽመው ያለፉ ቁጥር የለሽ ኢትዮጵያውያን፥ ለዛሬው ትውልድ ከነስማቸው እንዳልነበሩ ሆነዋል። በተከታታይ ትውልዶች ዘንድ ከቀረባቸው ተገቢ ዝና፥ ክብርና ሞገስ ይበልጥ የሚያስቆጨው፥ እንዳልነበር ሆኖ አብሯቸው ሲጠፋ የኖረው የአርአያነታቸው ቅርስ ነው። ይህም፥ በየፈርጁ ላለው ለዛሬው ኋላ ቀርነታችን አንድ ምክንያት መሆኑ ግልጽ ይመስላል።

ይህን ሐቅ ተገንዝቦ የመጀመሪያውን የመለወጥ ሙከራ ያደረገ ኢትዮጵያዊ ምሁር ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ነበር ማለት ይቻላል። የዛሬ ሰባ ስምንት ዓመት ገደማ (በ1915)፥ "የሕይወት ታሪክ (*Biographie*) በኋላ ዘመን ለሚነሡ ልጆች ማስታወቂያ" የተሰኘውን፥ የበርካታ ዘመነኞቹንና የቀደምቶቹንም የሕይወት ታሪክ ባጫጭሩ ለማቅረብ የሚቃጣ ሥራ አቅርቦ እናገኛለንና። ይህን ለማድረግ የተነሣውም በሙሉ ግንዛቤ የነበረ መሆኑን፥ በመጽሐፉ "መቅድም" ውስጥ የሚከተለውን ስናነብ እንገነዘባለን።

> . . . በዚህ ሁሉ ዘመን ውስጥ በኢትዮጵያ፥ ከቤተ መንግሥትና ከቤተ ክህነት ወገን እንደ ጊዜው ብዙ ዕውቀት የነበራቸውና፥ ለመንግሥታቸው ብዙ ሥራ የሠሩ እጅግ ብዙ ሰዎች ሳይኖሩ አይቀሩም ነበረ። ነገር ግን፥ እንደ ዛሬ ዘመን ነገሩን ሁሉ እየጻፉ ማስቀመጥ አልተለመደም ነበረና፥ ስማቸው በታሪክ ተጽፎ ያገኘናቸው ጥቂቶች ናቸው . . . በአውሮጳም ቀድሞ እንደዚሁ ነበረ።. . . ግን ዕውቀት እየሰፋ ስለ ሔደ . . . ለመንግሥታቸው መልካም ሥራ የሠሩትንና የብልሃት ሥራ ያወጡትን ሰዎች፥ የኋላ ልጆች እንዲያውቋቸው እያሉ መልካቸውን በፎቶግራፍ እያነሡ ታሪካቸውን በመጽሐፍ እየጻፉ . . . ማቆየት ጀመሩ። ይህ መጽሐፍ . . . ቢዮግራፊ ይባላል . . . የሕይወት ታሪክ ማለት ነው። . . . እኔም ይህን ቢዮግራፊ የሚባለውን መጽሐፍ ስለአየሁና ስለአነበብሁ፥ የሀገሬን የኢትዮጵያን ትልልቆች

> ሰዎች ከቀድሞ ጀምሮ የነበሩትን ስማቸውንና ታሪካቸውን ምንም እንኳ ፈጽሜ ባላውቀው፥ ከብዙ በጥቂቱ ከሙሉ በከፍሉ ከረዥሙ ባጭሩ አድርጌ ለመጻፍ ጀመርሁ . . . ."[1]

ይሁን እንጂ፥ ጸሐፊው እንዳሰበው "በጣም ታርሞ እንደገና" ከአምስት ዓመት በኋላ (1920) ሁለተኛው እትም ሳይወጣ ስለ ቀረ፥ እንዲሁም የእሱን ፈር ተከትሎ የቀጠለ ባለመኖሩ ውጥኑ ባጭር ተቀጨ::

ያ ትጉህና ንቁ ምሁር፥ እንዳቀደው ሰፊውን ሥራ ለመሥራት በተለያዩ አጥጋቢ ምክንያቶች ባይችል እንኳ፥ 'እንዴት የራሱን የተሟላ የሕይወት ታሪክ ጽፎ ቅርስ ሳይተውልን ሔደ?' የሚለው ጥያቄ መቼም ትክክለኛ መልስ ሳያገኝ አብሮን የሚኖር ጥያቄ ነው:: ሆኖም፥ "የትልልቆቹን ሰዎች ታሪክ ሳላስቀድም የራሴን ልጽፍ?" የሚል ሳይሆን ይቀራል?

የዚች አጭር ጽሑፍ ርእሰ ጉዳይ የሆኑት፥ ክቡር ዶክተር ሐዲስ ዓለማየሁም፥ (የዶክተር ክዋሜ ንክሩማ፥ የጁሊየስ ኔሬሬና የካውንዳም የክብር ዶክተርነት መሆኑን ልብ ይሏል) የሕይወት ታሪክ መጻፍን ፋይዳ የሚያውቁና፥ የራሳቸውን የግል ሕይወት ታሪክ ለመጻፍ ዐቅሙም ጊዜውም የነበራቸው ናቸው:: ነገር ግን አላደረጉትም:: በራሳቸው ተነሣሽነት አለመጻፍ ብቻ ሳይሆን፥ በብዙ ሌሎች ሰዎች ተለምነውም፥ ተጎትጉተውም በጄ አላሉም::

ከሦስቱ ዐበይት ልብ ወለድ *ሥራዎቻቸው* አንዱ፥ *የልምዣት*፥ በ1980 ሲታተም፥ በዚች ጽሑፍ አቅራቢ እንኳ ተደጋግሞ የቀረበላቸው ጥያቄ፥ የግል የሕይወት ታሪካቸውን "ለምን አይጽፉልንም?" የሚል ነበር:: የዘወትር መልሶቻቸው ፍሬ ሐሳብ፥ "ይኸን ማድረግ የሚችሉና (ተገቢም የሚሆነው) ለሰው ልጅ የበጀ ትልቅ ሥራ የሠሩ ናቸው:: እኔ ምን ሠራሁ ብዬ ነው ይኸን የማደርገው?" ነው:: የ"ጻፉልን" ጥያቄው ግን ከብዙዎች ይቀርብላቸው እንደ ነበር አይጠረጠርም::

ከነዚህ አንዱ፥ *መንግሥቱ ለማ*፥ ለራሱ የግል ሕይወት ታሪክ ጽፈት መነሻ፥ ነሐሴ 27 ቀን 1972 በጻፈው "*መንደርደሪያ*" ውስጥ የሚከተለውን እናነባለን፤

> . . . . በኢትዮጵያ *ሥነ-ጽሑፍ*፥ የሕይወት ታሪክ (*Biography*)፥ የግል ማስታወሻ (*Diary*) *ሥነ* ጽሑፍ እምብዛም አልተስፋፋም:: ያሉን ጥቂቶች ናቸው:: 'ሐተታ ዘርዓ ያዕቆብ'፥ 'መጽሐፈ ትዝታ'፥ 'የታሪክ ማስታወሻ'፥ 'ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ' ናቸው፥ እኔ የማውቃቸው:: የፈታውራሪ ተክለ ሐዋርያትና የራስ እምሩም አለ ይባላል::

አቶ ሐዲስ ዓለማየሁን ሽንጎ ሳለን የራሳቸውን ግለ ታሪክ እንዲጽፉ ደጋግሜ አሳስቤያቸው ነበር። ከምን እንደደረሱ አንድ ቀን ሔጄ መጠየቅ አለብኝ።

እስከዚያ ግን የራሴን ከወረወርኩ ፊሪ አልባልም. . . .[2]

ይሁንና፥ የብዙ ሰዎች ውትወታና ግፊት ሙሉ ለሙሉ ባይሳካም፥ በ1985 ለታተመችው *ትዝታ* ለተሰኘችው ለሐዲስ ዓለማየሁ መጽሐፍ ተፀንሶ መወለድ አስተዋጽኦ አድርጓል ብለን እናምናለን።[3] እርግጥ፥ *ትዝታ* ከሐዲስ ዓለማየሁ የሕይወት ሰባት ምዕራፎች በሦስተኛውና አጠር ባለው የዕድሜያቸው ክፍል ላይ ብቻ ነው ያተኰረው። ሆኖም፥ የሐዲስን አስተሳሰብ አድማስ ስፋት ለማሳየትና ለኢትዮጵያ የዚያን ወቅት ታሪክ ጽሒፈት ያከለው ቁም ነገር ያለው የዐሥር ዓመት ያህል የሕይወት ምዕራፍ ጽሑፍ ነው። የዶክተር ሐዲስ ዓለማየሁን መጪ ሕይወት አግጣጫ የለወጠ ወሳኝ የሕይወት ምዕራፍም ነበር። ይኸን በቦታው እንመለስበታለን።

የሕይወት ምዕራፎቻቸው ያልናቸው የሚከተሉትን ነው፤

| | |
|---|---|
| ፩፥ ከልደት እስከ ቅኔ መቀኛትና ቅጸላ | (1902-1918) በጎጃም። |
| ፪፥ ዘመናዊ ትምህርትና መምህርነት | (1918-1927) በአዲስ አበባና በጎጃም |
| ፫፥ ዘመቻ፥ አርበኝነትና ግዞት | (1928 - 1936) በኢትዮጵያና በኢጣልያ |
| ፬፥ በመንግሥት ሥራና ከፍተኛ ኃላፊነት | (1936-1966) |
| ፭፥ አብዮቱና ሐዲስ ዓለማየሁ | (1966-1968) |
| ፮፥ ደራሲ ሐዲስ ዓለማየሁ | (1948-1983) |
| ፯፥ ድኅረ ዘመነ ደርግ | (1983-) |

ለዚች ጽሑፍ አቀራረብም ከሌላው ይልቅ ይኸንኑ ቅደም ተከተል መያዙ ለዓላማችን ተስማሚ ሆኖ አግኝተነዋል። በማንኛውም የዕድሜ እርከን የሚገኝ አንባቢ የራሱን ሕይወት ለማያ የሚያግዝ መስተዋት ሊሆነው ይችላልም ብለን እናስባለንና።

የሐዲስ ዓለማየሁ ሦስተኛና ከሁሉም ረዥሙ ልቦለድ በ1980 ሁለት ጊዜ ተከታትሎ ሲታተም፥ የደራሲውን ሁለት የተለያዩ የልደት ዘመኖች በየሽፋኑ ጀርባ ላይ ይዞ ለሕዝብ ቀርቦ ይገኛል። በጥር ወር፥ በሃምሳ ሺ ቅጅዎች የወጣው *የልምዣት* የመጀመሪያ እትም፥ "ደራሲ ሐዲስ ዓለማየሁ፥ ጥቅምት 7

ቀን 1906 በጎጃም ክፍለ ሀገር፥ በደብረ ማርቆስ አውራጃ፥ በጎዛምን ወረዳ እንዶዳም ኪዳነ ምሕረት ተወለዱ" ይላል። ይኸ በ1978 የወጣውን የወንጀለኛው ዳኛን ሦስተኛ እትም ፈር የተከተለ ነው። በግንቦት ወር፥ ርእሱ የእልም እዣት ሆኖ በሃያ አምስት ሺ ቅጅዎች የወጣው ደግሞ፥ ከላይ የጠቀስነውን ሁሉ ይዞ፥ በደራሲው የተረጋገጠውን ትክክለኛ የልደት ዘመን በመተካት 1902 ብሎ አውጥቷል። ስለዚህ፥ ምንም እንኳ ከ1980 በፊት በወጡ ደራሲውን በሚመለከቱ ሰነዶች ውስጥ ሁሉ 1906 ተመልክቶ የሚገኝ ቢሆንም፥ ስህተት መሆኑንና፥ ትክክለኛው ዘመን 1902 መሆኑን ይገነዘቧል።[4]

የሐዲስ የልደት ቦታ እንዶዳም፥ የእናታቸው የወይዘሮ ደስታ ዓለሙ ሀገር ስትሆን፥ የአባታቸው የዓለማየሁ ስሎሞን ደግሞ፥ በማቻክል ወረዳ የሚገኘው ኤልያስ ነው። እነዚህ ኩታ ገጠም ወረዳዎች በደብረ ማርቆስ አውራጃ ውስጥ ቢሆኑም፥ ጎዛምን ወረዳ ዋና ከተማው፥ እንደ ክፍለ ሀገሩና እንዳውራጃውም፥ ደብረ ማርቆስ ነው። የማቻክል ግን አማኑኤል የሚባለው ከተማ ነው። እንዶዳም ከደብረ ማርቆስ ውሎ ገባ መንገድ ርቀት ላይ ነው። በሌላ በኩል፥ የእንዶዳም ሰዎች በአንጻራዊ ደረጃ ተለቅ ወደሚለው ኤልያስ አምባ ገበያ እየሔዱ ይገበያያሉ።

ዓለማየሁ ስሎሞን እንዶዳም መጥተው፥ በኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ሲያገለግሉ ወጣቷን ደስታ ዓለሙን አጭተው ያገባሉ። ደስታ፥ ባካባቢውና በእንዶዳም አምባ የታወቁትና ተሰሚነት የነበራቸው፥ የዜማ መምህሩ የዓለሙ ሥዩም ልጅ ናቸው። ተሰሚነት ያላቸው መሆኑ፥ ባንድ ወቅት ለእንዶዳም ኪዳነ ምሕረት ገዳም አበ ምኔትነት ተመድበው የመጡትን፥ 'ዘመናዊና ዓለማዊ መሳይ ነውና' አይገባም ብለው ማስነሣት በመቻላቸው ብቻ እንኳ ይታያል። በዜማ መምህርነታቸውም በኩል፥ ራሳቸው ዘንድ ቀጥታ ለመማር ከሚመጡት ሌላ፥ ከሌላ መምህር ዘንድ ተምረው ብቃታቸውን ለማስመስከር እሳቸው ዘንድ የሚመጡ እንደ ነበሩ የልጅ ልጃቸው ያስታውሳሉ።

የዓለማየሁ ስሎሞንና የደስታ ዓለሙ ጋብቻ አንድ ፍሬ ያስገኛል - ሐዲስን። ሆኖም ዓለማየሁ ስሎሞን ለረዥም ጊዜ እንዶዳም ሳይቆዩ፥ እድገት ፍለጋ፥ በኢሉባቦር ክፍለ ሀገር ወደ ቡኖዋቤኮ ይሔዳሉ። እናት ሕፃኑን ሐዲስ ዓለማየሁን ይዘው አባታቸው ቤት ይመለሳሉ። ወጣቷ ወይዘሮ የልጅነት ባላቸውን (ፍቺ አልነበረምና) ለረዥም ጊዜ ጠብቀው፥ ኋላ እንደገና አግብተው ሌሎች ልጆች ይወልዳሉ።

አንድ ለአባቱ የሆነው ሐዲስ ግን የዜማ መምህር ከሆኑት አያቱ ቤት ያድጋል። ዕድሜው ለትምህርት ሲደርስ፥ ከሞቀ ቤቱ ተቀምጦ ፊደል ይቆጥራል፥ ዳዊት

ይደግማል፥ ዜማ ይማራል፡፡ ይኸን ሁሉ የሚያገኘው ከገዛ አያቱ ከዓለሙ ሥዩም ነው፡፡

ታዳጊው ሐዲስ ግን ይኸን ዕድለኛነቱን ሳይሆን የሚያየው፥ እንደ እኩዮቹ ከቤት ርቆ ሔዶ ቀኑን ሙሉ እንደ ልቡ ሲጫወት ለመዋል አለመቻሉን ነበር፡፡ እንደ አባት የሚያያቸውና "አባባ" የሚላቸው አያቱ፥ ካህን ዓለሙ ሥዩም አንድ ልማድ ነበራቸው፡፡ ምሣ ከተበላ በኋላ፥ በግቢያቸው በሚገኘው አትክልት ውስጥ ከጥላ ቦታ አስነጥፈውና መጠጊያ (መከዳ) አስደርገው፥ ሐዲስን ትምህርቱን ያስቀጥላሉ፡፡ ከምግብ በኋላ መሆኑና ከውሎአቸው መገላገሉም ዘና አድርጎ እንቅልፍ ሲያሸልባቸው፥ ጨዋታ ፍለጋ ወደ ከብት እረኞች ዘንድ እብስ ይላል ሐዲስ፡፡ የሚጠብቀው ቅጣት (በቁንጥጫ መለምዘግ) ትዝ የሚለው፥ ማታ ሲመለስ ወደ ቤት ሲቃረብ ነበር፡፡ ቅጣቱን ተቀብሎ 'አይለምደኝም' ብሎም፥ ነገም ተነገ ወዲያም ያው ነበር፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ፥ የእረኞቹ ልዩ ልዩ ጨዋታ ተሳታፊ ለመሆን፥ የነሱ ታዛዥና ፈቃድ ፈጻሚ መሆን የግድ ነበር፡፡ "ሒድ ያቺን ላም ወደዚህ መልስ"፥ "ያቺን ጥጃ እንደዚህ አድርግ"፥ ለነዚህ ሁሉ 'እሺ' ማለት አለ፡፡ ዐልፎ ዐልፎ ግን መጣላትም አለ፡፡ በዚህ ላይ ነው ቅጣቱ የሚጨመር፡፡ ታዳጊው ሐዲስ፥ ከቅጣቱም በእረኞች ከመታዘዙም በጫወታቸው መሳተፉ ስለሚልቅበት ሁሉንም ችሎ ይቀበል ነበር፡፡

በየካቲት ወር 1984 ለመጀመሪያና ለመጨረሻ ጊዜ ታትሞ የወጣው ፍካሬ የተሰኘው መጽሔት፥ የመጀመሪያ እንግዳው አድርጎ የነበረው አረጋዊውን ክቡር አቶ ሐዲስ ዓለማየሁን ነበር፡፡ የመጽሔቱ ዓላማ፥ የሕይወት ታሪካቸው አስተማሪነትና አርአያነት አላቸው የሚባሉትንና፥ የሀገር ፍቅራቸው በተግባር እሳት የተፈተነውን አረጋውያን፥ ከአዲሱ ትውልድ ጋር ማስተዋወቅ ይመስላል፡፡ የዜና መጽሔት የነበረ በመሆኑ ግን፥ ብዙ ዝርዝር ውስጥ አይገባም፡፡ ሆኖም፥ አንዳንድ ሐቆችን ከቃለ ምልልሱ በመነሣት አስፍሮ ይገኛል፡፡ ከዚህ በላይ ስላነሣነው የሐዲስ የሕይወት ገጽታ መጽሔቱ ውስጥ የሚከተለው ይነበባል፤

> '. . . በዚህ በእረኝነት ዕድሜያችን ነው ትልልቆቻችን የሚሠሩትን እያስመስልን የምንጫወተው፡፡ የእርፍ አያያዙን፥ የጠመንጃ አጎራረሱንና አነጣጠሩን፥ የዳኛ ወንበር አቀማመጡን፥ የዲያቆን አቋቋምና የድምፅ አጣጣሉን፥ በአጠቃላይ የማህበራዊ ተሳትፎን በየገጹ እንደ ቲያትር ሚና ይዘን እየሠራን መጪውን ሕይወት ሆነን የምንገኘው' አሉን፡፡[5]

መጽሔቱ ያስፈረውና፥ ከዚያ ቀደም ብዙዎቻችን የማናውቀው የነበረ አንድ ነገር እናነባለን፡፡ ይኸም ስላጎታቸው ስለ በላይ ዘለቀ ነው፡፡ መጽሔቱም እንደጠቆመው፥ ጎጃምና በላይ ዘለቀ ባንድነት ሲነሣ፥ አንባቢ ሁሉ በታሪክ

የምናውቀውን አባ ኮስትርን ነው ወዲያው በአእምሮው የሚያመጣው። መጽሔቱ ግን ይቀጥላል፤

> . . . የሐዲስ ዓለማየሁ አጎት ደጃች በላይ ዘለቀ ግን ሌላ ናቸው። ስመ ሞክሼ መኮንን ነበሩ። ብዙ ወታደር፥ ብዙ ወገን የሚያሳድሩ። ሐዲስ ዓለማየሁ በዚያ ለጋ ዕድሜያቸው ከአጎታቸው ዘንድ የመኳንንቱን የቤትና የአደባባይ አስተዳደር፥ የወታደሩን ትጥቅና አለባበስ፥ የሥልጣን የክብር ደረጃ አመዳደብና ተዋረድ ደህና አድርገው ዐውቀዋል። በተለይ በዕድሜ ወጣት የሆነው የወታደሩ ክፍል ስሜታቸውን ይስብ ነበር።[6]

መጽሔቱ ሐዲስን እንደሚከተለው ይጠቅሳቸዋል፤

> . . . እኔ ግን አብሬ መጫወት የምፈልገው ከታዳጊ ወጣት ወታደሮች ጋር ነው። እነዚህ በባህል አጠራር 'ጋሜ' ይባላሉ። ከተቀሩት ለመለየት ጸጉራቸውን ጋሜ ይላጫሉ። እኔም እነርሱን ለመምሰል ጋሜ ተላጭቼ እቀላቀላቸውና እጫወት ነበር። በዕድሜም በጣም ስለምንቀራረብ እንግባባ ነበር። ሁኔታው የመኳንንቱን አስተዳደር በተሣትፎ እንዳውቅ ዕድል ሰጠኝ።[7]

በዚህ አኳኋን፥ በቤት የቀለም፥ በውጭ የማህበራዊ ኑሮ ትምህርት እየቀሰመ በእናቱ ቤተ ዘመድ መካከል፥ በአያቱ ቤት የልጅነትና የታዳጊነት ዘመኑን፥ እንዲሁም የሀገራችንን ትምህርት ከዳዊት ደገማ እስከ ጾመ ድጓ ዜማ፥ ከእንዶዳም ሳይወጣ አጠናቀቀ። ከዚያ፥ የቅኔ ትምህርት ፍለጋ ወደ አባቱ አምባ፥ ወደ ደብረ ኤልያስ አመራ። በሁለት ዓመቱ ግድም የተለዩት አባቱ ካህን ዓለማየሁ ሰሎሞን ግን እዚያ አልነበሩም። እንዶዳምን ብቻ ሳይሆን፥ ጎጃምን ለቅቀው ከሔዱ ከዐሥር ዓመት በላይ አልፏል። ይሁን እንጂ፥ ኤልያስ የአባቱ ቤተ ዘመድ የሚገኝበት አገር ከመሆኑም በላይ፥ የአባቱ ቤት በእህታቸው ጠባቂነት ያለ ስለ ነበረ፥ አክስቱ ዘንድ ተቀምጦ፥ የቅኔ ትምህርቱን ከመምህር ገብረ ሥላሴ መቅሰም ጀመረ። ሆኖም፥ በደብረ ኤልያስ ምንም ያህል ሳይቆይ፥ ከትምህርት ጓደኞቹ ጋር ወደ ሌላ ቦታ ለመሔድ መከሩ። ዋናው ምክንያታቸውም፥ 'ቅኔ መማር በቤተ ዘመድ መካከል ተቀምጦ አይደለም። ትምህርቱም የሚገባው፥ ጣዕሙም የሚታወቀው፥ ከዘመድ ርቆ ሔዶ በቀፈፋ እየኖሩ ሲማሩት ነው' የሚል ዐይነት ነበር።

በዚህ መሠረት ወደ ደብረ ወርቅ ለመሔድ ይቆርጣሉ። ደብረ ወርቅ የሚገኘው ለደብረ ማርቆስ አውራጃ፥ የሰሜን ምሥራቅ አዋሳኝ በሆነው፥ በብቸና አውራጃ ውስጥ፥ በእናርጅ እናውጋ ወረዳ ነው። ሆኖም፥ ከደብረ ኤልያስ እስከ ደብረ ወርቅ ጉዞው የግር ስለሆነ፥ በተለይ ከእንዶዳም ብዙ ርቆ ከዚህ ቀደም ሔዶ

ለማያውቀው ዐሥራ አራት ዓመት ዕድሜ ያህል ለሆነው ሐዲስ ቀላል ርቀት አልመሰለም ነበር። ከሚያውቁት ሁሉ መራቃቸውም ነበርና።

አሁን፥ የቅኔ ትምህርቱና ቦታው የራሱ ምርጫና ውሳኔ በመሆኑም ይሁን፥ በዕድሜ ከፍ ማለቱ፥ ሐዲስ በትምህርቱ ትጋት ያሳያል። በዕድሜና በአካል ከጓደኞቹ አነስ ብሎ በመታየቱ፥ አብዛኛውን ጊዜ ቁራሽ ልመናውን ተለቅ ያሉት ሲያደርጉ፥ ሐዲስ ጎጆና ሰፈር ጠባቂነት ዐይነተኛ ድርሻው ይሆናል። ከዕለታት ባንዱ ቀን በአካባቢው ትልቅ ድግስ ይኖርና፥ ተማሪም መምህሩም ሁሉ ሔዶ፥ ሐዲስ ሰፈር ይቀራል። ቅኔውን ሲቆጥር ቆይቶ የተዋጣ ስለመሰለው የሚነግረው ሰው ቢፈልግ በአካባቢው ያጣል። በኋላ፥ እራሳቸው ወደ ድግሱ ያልሔዱትን ዋናውን መምህር ያይና፥ ለሳቸው ቅኔውን ለማቅረብ መብት እንደሌለው (ማለትም ደረጃው እንደማይፈቅድ) ሳያስተውል፥ ቶሎ ለመንገር ወደሳቸው ይጣደፋል። ታላቁ መምህርም ልጅነቱንና ድፍረቱን አይተው ይሁን አይታወቅም፥ ይፈቅዱለትና ያቀርባል። በቅኔው የተደነቁ የመሰሉት መምህር፥ ከወዴት እንደ መጣ ሲጠይቁት፥ ደስታ ተሰምቶት የነበረው ሐዲስ፥ "ከደብረ ኤልያስ ነው የመጣነ" ብሎ ስለ ጓደኞቹ ጭምር ይመልሳል። ከታላቁ መምህር ያገኘው ምላሽ ግን ታዳጊውን ቅኔ ተማሪ የሚያስደነግጥ ነበር።

"አንቺም ጓደኞችሽም ቶሎ ከዚህ ጥፉ! ወደ ዲማ ሒዱ!" ይሉታል። ግራ እንደ ተጋባ ጎጆው ሔዶ ሲጠብቅ ጓደኞቹ ከሔዱበት ይመጣሉ። መርዶውን ሲነግራቸው፥ "ማን ከደብረ ኤልያስ ነን ብለህ ተናገር አለህ?" እያሉ ጓደኞቹ ደግሞ በተራቸው ወረዱበት። ሐዲስ ነገሩ ሊገባው አልቻለም። እንቆቅልሹ የተፈታለት በኋላ ነበር።

ኤልያስና ዲማ ('እንደ ደብረ ሊባኖሶች፥ አንኮበሮች፥ አዘዞች፥ ዋልድቦችና አክሱሞች') የተዋሕዶ እምነት ተከታዮች ሲሆኑ፥ ደብረ ወርቆች ደግሞ የቅባት እምነት ተከታዮች ነበሩ። ስለዚህ፥ ታላቁ የደብረ ወርቅ መምህር አለቃ ይሄይስ፥ እነ ሐዲስ ከየት እንደ መጡ ሲረዱ፥ ስለ ጉዳዩ በቅጡም ወይም ጨርሶ ምንም የማያውቁትን ትምህርት ፈላጊ ታዳጊዎች ከደብረ ወርቅ ያሰናብቷቸዋል።[8] ምርጫ ያልነበራቸው ልጆችም ወደ ዲማ ይሔዳሉ። ዲማም የሚገኘው በዚያ አውራጃ ብቻ ሳይሆን ወረዳውም እናርጅ እናውጋ ነው። ሐዲስ በዝነኛው የቅኔ ትምህርት ቤት ቅኔውን ይያያዘዋል። ትጋቱም ይጨምራል። በመሆኑም አጠር ባለ ጊዜ ተቀኝቶ፥ የውዳሴ ማርያም ትርጓሜ ትምህርት ይጀምራል። የዚህ ትምህርት መምህር፥ አለቃ በላይ የሚባሉ የሸዋ ተወላጅ ነበሩ። ተማሪዎቹ ትምህርታቸውን ገና ሳያጠናቅቁ አለቃ በላይ ካገሬው ካህናት ጋር ጠብ ያበቅላሉ። ጠቡ እስከ ድብድብ የዘለቀ የነበረም ቢሆን፥

መምህሩ ጥለው እንዳይሔዱ ሽማግሌና ገላጋይ ይገባበታል። በዚህ መሐል አለቃ በላይ ከወዳጆቻቸው ጋር ይጻጻፉ ነበርና፥ ባንድ ፊት የዚያን ውጤት፥ በሌላ በኩል የሽምግልናውን ጉዳይ ለመከታተል፥ ገለል ብለውም ለመቆየት፥ አባይን ተሻግረው ሰላሌ ውስጥ፥ በጥንታዊቷ የማርያም ሰበካ፥ በዐለተ ማርያም (የማርያም አልጋ) ይቀመጣሉ። ሐሳባቸው ከሁለቱም አግጣጫ የሚሆናቸው ካልመጣ ወደ አዲስ አበባ ለመዝለቅ ነበር። ከዲማ ሲነሡ፥ ሐዲስ እና ሌሎቹ አምስት ተማሪዎቻቸው አብረዋቸው ተነሡ። እመንገድ ትምህርታቸውን እየቀጠሉ መጥተው ዐለተ ማርያም አብረው ተቀመጡ።

ከሦስት ወራት ያህል ቆይታ በኋላ፥ አለቃ በላይ ከአዲስ አበባ ሹመት አግኝተው ወደ ደብረ ብርሃን ሲሔዱ፥ ልጆቹ ብቻቸውን ወደ አዲስ አበባ ይዘልቃሉ። ያኔ ጉዞው ሁሉ በግር ስለ ነበር፥ በቆሎ ተማሪ ደንብ በቀፈፉ ምግባቸውን እያገኙ ተማሪዎቹ ከቀናት በኋላ አዲስ አበባ ደርሰው፥ ማረፊያቸውን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ያደርጋሉ። ቤተ ክርስቲያኗ ካቡኑ መኖሪያ ጋር የተያያዘች ስለሆነች፥ ከየቦታው ለመካን፥ የዲቁናና የቅስና ማዕርግ ለመቀበል የሚመጡ ሁሉ መናኸሪያ ስለ ነበረች፥ ምንም እንኳ 'ላገሩ ባዳ፥ ለሰዉ እንግዳ' እንደሚባለው የነበሩ ቢሆንም፥ የእንደነዚያ ዐይነት ሰዎች በብዛት መኖር አረጋጊ ሆኖላቸው ነበር ማለት ይቻላል።

የነዚህ ተማሪዎች ዓላማም አዲስ አበባ ለመኖር ሳይሆን፥ በጎጃምና በአዲስ አበባ መካከል እየተመላለሱ ከሚነግዱ የሲራራ ነጋዴዎች ጋር አብረው ወደ ሀገራቸው ለመመለስ ነበር። በዚያን ዘመን (1918)፥ መንገድም ድልድይም አልነበረም። ወደ ጎጃም ለመሔድ በግር ተጉዞ፥ አባይን በዋና ተሻግሮ ስለ ነበርና፥ እንዲሁም በርከት ብሎ ተሰባስቦ እንጂ በተናጠል የማይሞከር የነበረ በመሆኑ፥ ነጋዴዎቹን ማግኘት የግድ ነበር። ሆኖም፥ ነጋዴዎቹን ሳያገኙ በማነህ ማነህ ዐሥራ አምስት ቀን ያልፋል።

ይሁን እንጂ፥ ሐዲስና ጓደኞቻቸው ሥራ አልፈቱም ነበር። ቀን በቀን ከተማውን ሲዞሩና 'ትንግርት' የሚመስሏቸውን 'የከተማ'፥ እንግዳ ነገሮች ሲያዩ ይውላሉ። አንድ ቀን፥ አራዳ (ኋላ ጣልያን መጥቶ ፒያሳ ብሎ የዛሬ ስሙን አወጣለት አካባቢ) ያሉትን ሱቆች እየዞሩ ሲመለከቱ፥ በሱቁ መስተዋት በኩል ዳቦ የተደረደረበት አንድ መስኮት ያያሉ። ቀልባቸውን ይስበውና ወደዚያው ተጠግተው ቆመው በአግራሞት ሲመለከቱ፥ አንድ ሰው ቀርቦ ያነጋግራቸዋል። እንደ ጠረጠረው ከጎጃም መሆናቸውን አረጋግጦ፥ ፍላጎታቸውንም ገምቶ ወደ ምግብ ቤቷ ውስጥ አስገብቶ ያዩት የነበረውን ፉርኖ (ዳቦ) እንዲቀምሱት ሻይም እንዲጠጡ ይጋብዛቸዋል። ይኸን ከዚህ ቀደም አይተውት እንኳ የማያውቁትን ነገር በመቅመሳቸው ልዩ የደስታ ስሜት ያድርባቸዋል። ይህ ሰው፥ ኋላ

እንደተረዱት፥ የዕውቁ ባለቅኔና የቲያትር ደራሲ፥ የዮፍታሄ ንጉሤ ወንድም፥ አያሌው ንጉሤ ነበር። ቀደም ሲል ከጎጃም የትኛው አካባቢ እንደሆኑ ሲነጋገሩ ከኤልያስ መሆናቸውን አንዱ ተናግሮ ስለነበር "እነማን ታውቃላችሁ?" ሲባል አጥጋቢ መልስ ሊሰጥ የቻለ ሐዲስ ብቻ ነበር።

ስለ ወደፊት ሐሳባቸው ሲጠየቁ ደግሞ፥ ነጋዴ ሲያገኙ ወደ ሀገራቸው ለመመለስ መሆኑን ሲሰማ፥ አያሌው ንጉሤ ሐሳባቸውን ቀይረው 'ፈረንጅ' ተማሪ ቤት፥ ዘመናዊ ትምህርት እንዲማሩ ማድረግ ቢችል ይፈቅዱ እንደሆነ ይጠይቃቸዋል። የቀሩት በደስታ እሺ ሲሉ፥ ሐዲስ ብቻ እምቢ ይላል። በዚህ ጊዜ ሐዲስ የ16 ዓመት ወጣት ነው። የስዊድን ሚሲዮን ተማሪዎች፥ መለዮ ልብሳቸውን ለብሰው፥ በሰልፍ ሆነው ፍል ውሃ ወርደው ለመታጠብ፥ በቅድስት ማርያም በኩል አልፈው ሲሔዱ ጓደኞቹ እያዩ ጎምጅተው ኖሮ፥ የተመኙትን በታምር እንዳገኙት ነበር የቆጠሩት። ስለዚህ፥ በቀጠሮ ቀን ሐዲስ እንዲሁ ከጓደኞቹ ጋር ሔደ እንጂ የመመዝገብ ሐሳብ አልነበረውም።

አያሌው ንጉሤም ያስተምርበት የነበረው የስዊድን ሚሲዮን፥ ከቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ጥቂት ከፍ ብሎ፥ ዛሬ መካነ የሱስ ቤተ ክርስቲያን አለበት ቦታ፥ አምስት ኪሎ ነበር። እዚያ እንደ ደረሱ አቶ አያሌው ልጆቹን ከቄስ ባድማ ጋር ያገናኛቸዋል። እሳቸውም ከትምህርት ቤቱ መሪዎች ጋር ይነጋገሩና ያስፈቅዳሉ። ይህ ከመሆኑ በፊት፥ ሐዲስ ከሌሎች በመነጠል ለምን ትምህርት ቤቱ ለመግባት እንዳልፈቀደ ለማጣራት ቄስ ባድማ ያለው ይጠይቁታል።

መልሱ፥ "እኔ ሃይማኖቴን መለወጥ አልፈልግም" ይሆናል። ትክክለኛ አባባሉ 'እኔ መኮትለክ አልፈልግም' የሚል ነበር።

ቄስ ባድማ እሳቸው ራሳቸው ቄስ መሆናቸውንና፥ ወጣቱን ሐዲስን ሃይማኖቱን የሚያስለውጠው ሰው እንደሌለ፥ ቁም ነገሩ የዘመኑን ትምህርት መማር መሆኑን በሰፊው በማብራራት ያግባቡታል።

ከጓደኞቹ መለየቱ ያሳሰበውና የገለጸውም ማራኪነት ልቡን መክፈል የጀመረው ሐዲስ፥ ሁለት የማጣሪያ ጥያቄዎች ያቀርባል። ጥያቄዎቹም፥ በሳምንት ውስጥ ዐርብ ዕሮብን፥ ፍልሰታንና ሁዳዴን (ዐቢይ ጾምን) መጾም የማይከለከል መሆኑንና፥ ውዳሴ ማርያምና ሌሎች ዕለታዊ ጸሎቶቹን ማድረስ መቻልን የሚመለከቱ ነበሩ። ለጥያቄዎቹ አጥጋቢ መልስ ያገኛል። ቄስ ባድማ፥ አጥር ግቢው ውስጥ ወደሚገኝ አንድ ዛፍ በጠቋሚ ጣታቸው እያመለከቱ፥ "'ያ ዛፍ ይታይሃል። በየቀኑ እሱን እየተደገፍክ እስኪደክምህ ድረስ መድገም ትችላለህ'

አሉኝ" ሲሉ አዛውንቱ ሐዲስ ለዚች ጽሑፍ አቅራቢ ባንድ ወቅት አጫውተውታል።

በዚያ ወቅት፥ ኦሌ ኤሪክሰን የሚባል ስዊድናዊ አስተማሪ እዚያ ነበር። ይህ ሰው አማርኛ ቋንቋ የሚያውቅና ወደ ሃያ የሚጠጉ መጻሕፍትና ጽሑፎች በአማርኛ ያሳተመ ነው። ከነዚህ መካከል፥ *ያንድ አራሽ ንግግር፥ ዓለምን እንይ፥ ለጥቅምና ለደስታ* እና *አሁንና ጥንት* የሚባሉት ይገኙባቸዋል። ከአውሮፓ ቋንቋዎችም ሃይማኖት ነክ የሆኑ ጽሑፎችን ወደ አማርኛ ተርጉሞ ወደ ዐሥራ ዘጠኝ ዐሥራዎቹ መጨረሻ ገደማና በ1920ዎቹ ውስጥ አሳትሟል። ስለዚህ፥ ስለ ኦሌ ኤሪክሰን የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ጠይቆ፥ ሐዲስ፥ "ትልቁ" ኤሪክሰን፥ "ትንሹ" ኤሪክሰን ተብለው ይለዩ የነበሩ መኖራቸውን እንጂ የትኛው በአማርኛ የሚጽፈው ኤሪክሰን እንደሆነ ያውቁ እንዳልነበረ ነግረውታል።

በስዊድን ሚስዮን የሚሰጠው ትምህርትም፥ ቋንቋውና ብዙዎች መምህራንም የውጭ ዜጎችና እንግዳ ነገር የነበሩ ቢሆንም፥ ለቅኔ ተማሪዎቹ ግር ማለትን እምብዛም አልፈጠሩም። እንዲያውም ትምህርታቸውን በንቃትና በትጋት እንዲከታተሉ ገፋፉዋቸው እንጂ። ይሁንና፥ በስዊድን ሚስዮን 1919ን ተምረው ሁሉም ወደ "መንግሥት" ትምህርት ቤት ተዛወሩ።

የመንግሥት ትምህርት ስንል፥ በትምህርት ሚኒስቴር የበላይ ጠባቂነት የሚተዳደር ለማለት እንጂ ኋላ እንደሆነው፥ ለሁሉም ወጣት ትምህርት በነፃ የሚሰጥበት ተማሪ ቤት ለማለት አይደለም። ምክንያቱም፥ ሐዲስና ጓደኞቹ ከስዊድን ሚሲዮን ሲወጡ የገቡት፥ ከሦስት ዓመት በፊት ሚያዝያ 17 ቀን 1917 እተከፈተው፥ "የተፈሪ መኮንን ተማሪ ቤት" ነበር። እዚያ ባዳሪነት ("በነዋሪነት" ነበር ያኔ ቃሉ) ለመማር ደህ መሆናቸውን አስመስክረው ከተፈቀደላቸው በስተቀር፥ የተቀሩት እየተከፈለላቸው ነበር የሚማሩት።

በክቡር አቶ አማኑኤል አብርሃም፥ *የሕይወቴ ትዝታ* (1992) በተሰኘው መጽሐፍ ውስጥ ስለ ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት የዚያን ዘመን ሁኔታ እንደሚከተለው ተገልጿል።

> ልዑል ራስ ተፈሪ መኮንን፥ አዲስ አበባ ላይ፥ 'የተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት' የተሰኘ ዘመናዊ ትምህርት ቤት አሠርተው፥ ሚያዝያ 17 ቀን 1917 ዓ.ም ተከፈተ። ዓላማቸው፥ አዲስ አበባ ውስጥ የሚኖሩት ብቻ ሳይሆኑ፥ ከመላዋ ኢትዮጵያ ወጣቶች ተልከውና አንድነት ተቀላቅለው ዘመናዊውን ትምህርት እንዲሳተፉ ማድረግ ስለነበረ፥ አያሌ አገረ ገዥዎች ለትምህርት የደረሱ ወንድ ልጆችን መርጠው ወደ አዲስ አበባ እንዲልኩ አዘዙ። በዚህ መሠረት፥ ደጃች ሀብተ ማርያምም ከወለጋ ልጆች እንዲልኩ ስለተጠየቁ፥

> ከመኖሪያቸው አቅራቢያ ከነበረው የትምህርት ቤት፥ አማርኛ፥ ፈረንሳይኛና እንግሊዝኛ ይማሩ ከነበሩ ልጆች መካከል 23 ተመርጠው እንዲላኩ ወስኑና፥ መኳንንቶቻቸው የየራሳቸውን፥ የቅርብ ዘመዶቻቸውንና የአሽከሮቻቸውን ልጆች አቅርበው፥ የተመረጡት በ1918 ዓ.ም በመስከረም ወር ከመስቀል በዓል በኋላ ወደ አዲስ አበባ እንዲሄዱ ዝግጅት ተደረገ . . . .የተከፈተው በሚያዝያ 1917 ቢሆንም፥ በአዳሪነት የገቡ ተማሮች ስላልነበሩ፥ የወለጋ ልጆች መጀመሪያዎቹ አዳሪዎች የመሆን ዕድል አገኘን። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ከአዲስ አበባም፥ ከዳር አገር የመጡ ሌሎች ልጆች በአዳሪነት ገቡ። በመጀመሪያ ምግቡ ሁሉ በየቀኑ በአልጋ ወራሽ ግቢ እየተሰናዳ ይላክልን ነበር . . . የአዳሪ ተማሮች ቁጥር እየበዛ ሲሄድ፥ ለማዕድ ቤት የሚሆኑ ቤቶች ስለተሠሩና ሠራተኞች ስለተቀጠሩ . . . .[9]

ተማሪዎቹ መላክ ብቻ ሳይሆን በላኪው እየተከፈለላቸው ይማሩ የነበረ መሆኑን ደግሞ የሚከተለው ጥቅስ ያረጋግጣል፤

> . . . ፊታውራሪ ቀንዓም ወደ አዲስ አበባ መጥተው ባላጋራ የሆኗቸውን መኳንንት (የወለጋ) ከሰሱ። ደጃዝማችም [ሀብተማርያም] ስለተጣሏቸው [በክሱ ምክንያት]፥ በ1918 ዓ.ም. በፊታውራሪ ቀንዓ አማካይነት ወደ ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ለተላኩ ወጣቶች ለያንዳንዳቸው በዓመት ይከፍሉ የነበረውን ዘጠና ብር ለማቋረጥ ወሰኑ። ከዚህ የተነሣም፥ በሐምሌ 1919 ዓ.ም የትምህርት ቤቱ ሲዘጋ ስድስት ልጆች እንዲወጡ ተደረገ። ከነርሱም አንዱ እኔ ነበርኩ . . . .[10]

ስድስቱ ተማሪዎች ክረምቱን እየተመላለሱ ለአልጋ ወራሹ እያዘኑ አመልክተው፥ ባልደረባም ብላቴን ጌታ ኅሩይ ተሰጥተዋቸው፥ ደጃዝማቹ ቢጠየቁ፥ 'የጠላቴ ወገኖች በመሆናቸው ገንዘብ ልከፍላቸው አልችልም' ይላሉ። በትምህርት ቤቱ የ1920 የትምህርት ዘመን መከፈቻ ዕለት አልጋ ወራሹ ሲመጡ፥ ልጆቹ እያለቀሱ እንደገና ችግራቸውን በግምባር አመልክተው፥ "እኛ እንከፍልላቸዋለንና ተመልሰው ይግቡ" ስላሉ ትምህርታቸውን ያለ ሐሳብ ሊቀጥሉ ቻሉ።[11]

ስለዚህ፥ ሐዲስና አምስቱ ጓደኞቻቸው ከሁለተኛ (የትምህርት) ዓመታቸው ፍጻሜ በኋላ፥ 'የተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት' ገብተው ትምህርታቸውን ለመቀጠል፥ የሚከፍልላቸው ሰው ያስፈልግ ነበር። ሁኔታዎችን በደምብ የሚያውቀው አያሌው ንጉሤ፥ ለልዑል ራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት እንደራሴ፥ ለቀኛዝማች ይመር የነዚህን እርሱ በሚያስተምርበት የስዊድን ሚሲዮን ትምህርት ቤት፥ ለሁለት የትምህርት ዘመንና ከአንድ ዓመት ተኩል ላላነሰ ጊዜ ያወቃቸውንና በቅርብ የተከታተላቸውን ልጆች ጉዳይ ያቀርባል። ቄስ ባድማ

ያለው ኋላ ኅዳር 6 ቀን 1923 በወጣው *ብርሃንና ሰላም* ሳምንታዊ ጋዜጣ እንደሚገልጹት ከሆነ፥ ቀኛዝማቹ የተጠየቁትን ሚና ለመጫወት የመጀመሪያቸው አልነበረም። ስለዚህ፥ ለልዑል ራስ ኃይሉ ሲያቀርቡ፥ የልዑል ራሱ መልሳቸው፥ በርትተው የሚማሩ "ከሆነ ደግ ነው፤ እንደ ደንቡ ከፈልላቸውና ይማሩ" የሚል ነበር።[12] ራስን 'ከሆነ' ያሰኛቸው ቀደም ሲል የገጠማቸው ነገር ነበር፤ በ1916 ከአልጋ ወራሹ ጋር ወደ አውሮፓ ጉብኝት ከመሔዳቸው በፊት፥ የወንድማቸውን ልጅና አምስት 'የአሽከሮቻቸውን' ልጆች፥ ጥቂት ቀደም ሲል ተከፍቶ በነበረው የስዊዲን ሚስዮን ትምህርት ቤት አስገብተው፥ "ልጆቹ የትምህርት ቤቱን ደንቦች ማክበር አቅቷቸው አንድ ባንድ ወጥተው" ቀርተዋል። ከጉብኝቱ ሲመለሱ ደግሞ፥ የተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት እንደ ተከፈተ፥ እንደ ደጃዝማች ሀብተ ማርያም ሁሉ፥ እሳቸውም ከጎጃም ዐሥር ልጆች ልከው ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት አስገብተው ነበር። ልጆቹ ብዙም ሳይቆዩ ወጥተው ተበታትነዋል። ስለዚህ፥ እነዚህም ከነዚያ የተለየ ስለ ማድረጋቸው እርግጠኛነት ባይሰማቸው አይገርምም። መሠረታዊ አመለካከታቸው ግን፥ የሚማር ከተገኘ ይከፈልለት የሚል የነበረ ነው።

አያሌው ያቀረባቸው ተማሪዎች ግን በሀገራችን ትምህርት በቅኔ የተመረቁ፥ በዘመናዊ ትምህርት አያያዛቸውም የታዩ፥ የተፈተኑ ስለነበሩ፥ ይሁንታ ማግኘቱ ከባድ የነበረ አይመስልም። በመሆኑም ስድስቱ ወጣቶች (ሐዲስ የ18ኛ ዓመት) ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት በአዳሪነት እየተከፈለላቸው በ1920 የትምህርት ዘመን ትምህርታቸውን ይጀምራሉ።

ከዚህ ከፍ ብለን እጠቀስነው *የሕይወቴ ትዝታ* ውስጥ፥ በትምህርት ረገድ፥ የተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት "የፈረንሳይና የእንግሊዝ" ተብሎ በሁለት ዘርፎች የተከፈለ እንደ ነበር፥ አማርኛ በሁለቱም ዘርፍ የጋራ እንደ ነበር ይጠቅስና፥ ከተማሪዎቹ ውስጥ ከሦስቱ ሁለቱ እጅ የሚመርጡት ፈረንሳይኛ፥ ምክንያቱም፥ አልጋ ወራሽ የተማሩት ቋንቋ ነው እየተባለ እንደ ነበር ይገልጻል። ከስዊድን ሚስዮን ተማሪ ቤት ለመጡት ለነሐዲስ ግን ምርጫ ውስጥ መግባት አላስፈለጋቸውም። ሚስዮን ሳሉ በተማሩበት በእንግሊዝኛው ቋንቋ ዘርፍ ገቡ። ከዚያ ውጭ ደግሞ የጋራ የነበሩ ትምህርቶች ነበሩ። በመጀመሪያዎቹ ዓመታት በተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት የግዕዝና የአማርኛ መምህር የነበሩት ብላታ መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ፥ በነበረው ሁኔታ አነሳሽነት፥ መጀመሪያ በአዘጋጁት ያማርኛ ሰዋስው መቅድም ላይ፥ ከቋንቋዎቹ ትምህርት በተጓዳኝ፥ ". . . ሥዕል፥ ጅምናስቲክ፥ ሌላም ተግባረ እድ (አናጢነትና ሸማኔነት. . .)" ይሰጡ እንደ ነበር ጠቅሰው፥ ". . . የትምህርቱ ሥራ በትጋት ይካሔድ ጀመር። ተማሪዎቹም ለእንግሊዝኛውና ለፈረንሳይኛው ትምህርት ከሌላው ሁሉ ይልቅ ይጣጣሩለት ነበር"[13] ይላሉ። የሚያስገርም

አይደለም። ያኔ ዋናው ጥረት የውጭ ቋንቋን የማወቅ ስለ ነበረ፥ ቅድሚያና ትኩረት እንዲሰጥ ይፈለግ ነበርና ነው።

እዚህ ላይ አንድ መረጃ ማቅረብ አስፈላጊ ይመስላል። ይኸውም በመጀመሪያ በሀገሪቱ የተቋቋመው የዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤትም (1901) ሆነ፥ የተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት (1917) እና ቀደም ብለው የተከፈቱት ሌሎች ትምህርት ቤቶች፥ በዘመኑ በነበሩ ሁኔታዎች ገፋፊነት የተነሣ፥ አጽንኦት የሰጡት የውጭ ቋንቋ ማወቅን ነበር። ለዚህ፥ በብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል *ዝክረ ነገር* ውስጥ ማስረጃ የሚሆን እናገኛለን። እነሆ፤

"በዚህች ትምህርት ቤት በፈረንሳዊ[ኛ]፥ በእንግሊዝ[ኛ]፥ በኢጣልያን[ኛ]፥ በአረብኛ ቋንቋ ትምህርት እንዲሰጥባት ደንብ አወጡ [ምኒልክ]" ይላል።[14] ሥዕል፥ ስልፍ፥ ጅምናስቲክና አማርኛም እርግጥ ይሰጡ ነበር። ግን ፍላጎቱና አጽንኦቱ የውጭ ቋንቋ ትምህርት መሆኑ ጉልህ ይመስላል። ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴም በመጽሐፋቸው (*ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ*) ቅጽ አንድ ላይ ጉልህ ማስረጃ ይሰጡናል። ስደት ላይ ሆነው፥ እስከ 1928 በነበረው ረዥም የአልጋ ወራሽነትና አምስት ዓመት የንጉሠ ነገሥት ዘመናቸው፥ ለሀገሬ ሠርቻለሁ ብለው በተለይ በቅጹ ምዕራፍ 12 ከዘረዘሯቸው 32 ተግባራት መካከል አንዱ ትምህርት ቤቶችን የሚመለከት ነው። እንደሚከተለው ገልጸውታል፤

> 11ኛ፥ የትምህርት ቤት በአዲስ አበባ አንድ የዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ብቻ ነበር እንጂ ሌላ ስላልነበረ፥ <u>በውጭ አገር ቋንቋ የሚናገሩ</u> ሰዎች ጥቂቶች ነበሩ።
>
> ከ1917 ዓመተ ምሕረት ጀምሮ ግን በአዲስ አበባና በሌሎችም በዋና ዋናዎቹ ከተሞች <u>የውጭ አገር ቋንቋ</u> *መማሪያ* <u>ትምህርት ቤት</u> ስለ አቆምን፥ ከዚህ በፊት ከነበሩት ትምህርት ቤቶች በቀር ለልዩ ልዩ ሚሲዮኖችም ፈቃድና እርዳታ ሰጥተን፥ <u>የቋንቋ ትምህርት ቤት</u> በያውራጃው ስለ ተከፈተ፥ በዚህም ላይ ወደ ውጭ አገር ብዙ ልጆች እየሰደድን ስለ ተማሩ፥ ብዙ ልጆች በየሚኒስቴሩ *መሥሪያ* ቤት ለመሥራት ችለዋል።[15] (የግርጌ መስመሮች በኛ የተጨመሩ)

ስለዚህ፥ ተማሪዎቹ የመረጧቸውን የውጭ ቋንቋዎች ጠንቅቀው ለማወቅ እንዲተጉ ከላይ ይኸን የመሰለ ድጋፍና ግፊት ነበረበት። ደግሞም የዕውቀት መክፈቻ ቁልፉም ቋንቋ ስለሆነ፥ መትጋታቸው አያስገርምም ማለታችን ለዚህ ነው።

የትምህርት ዓመቱ ሲፈጸም፥ በተፈሪ መኮንንም ሆነ በሌሎች አንዳንድ ትምህርት ቤቶች በመዝጊያው ቀን ወላጆችና እንግዶች በተሰበሰቡበት ልዩ ልዩ ዝግጅቶች ይቀርቡ ነበር። እነዚህ ትርኢቶች ተማሪዎች በአስተማሪዎቻቸው አገዛና መሪነት የሚያዘጋጁቸው ነበሩ። ከነዚህም ቲያትር ዋናው ነበር ማለት ይቻላል።

በተፈሪ መኮንን ትምህርት በመዝጊያው ሥነ ሥርዓት ላይ አልጋ ወራሹ አዘውትረው ይገኙ ነበር። በመዝጊያው ሥነ ሥርዓት ላይ ዐቢዩ ነገር ደግሞ፥ በሁለቱም የቋንቋ ዘርፎች በዓመቱ ብልጫ አግኝተው ከአንደኛ እስከ ሦስተኛ ለወጡ ሽልማት መስጠት ነበር። በዚህም ወቅት የትምህርት ቤቱ እንደራሴና ዋና አስተዳዳሪ እና የትምህርት ቤቱ ዳሬክተር ንግግር ያደርጋሉ። ከዚያ መዝሙር፥ ቲያትርና ልዩ ልዩ ትርኢቶች ይቀርባሉ፥ ይታያሉ፥ ይጎበኛሉ (ለምሳሌ ያናጢነት ውጤቶች)።

ከነዚህ ተግባራት የወጣቱ ሐዲስ ጎላ ያለው ተሳትፎ በመዝሙርና በቲያትር ነበር። ቲያትሮቹ የሚቀርቡት ብዙውን ጊዜ በፈረንሳይኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች መምህራን አዘጋጅነት ነበር። አሁን በሳል ወጣት የነበረው ሐዲስ፥ በእንግሊዝኛዎቹ ቲያትሮች ላይ በተዋናይነት በመጫወትና መዝሙሮች በአማርኛ በመድረስ በዝማሬውም ንቁ ተሳትፎ ያደርግ ነበር። ለምን በአማርኛ ቲያትር አናዘጋጅም የሚለው ሐሳብ በአማርኛ የቲያትር ድርሰት ለመጻፍ እና ለማዘጋጀቱ እንቅስቃሴ ግፊት ይፈጥራል።

ተፈሪ መኮንን ተማሪ ቤት በተከፈተበት ወቅት የትምህርት ቤቱ እንደራሴና ዋና አስተዳዳሪ ሐኪም ወርቅነህ እሸቴ፥ የትምህርት ቤቱ ዲሬክተር (ሙሴ) ቶማሲኒ ነበሩ። ለትምህርት ቤቱ በቆመው ደንብ መሠረት፥ እንደራሴው ትምህርቱን በሚገባ ለማስኬድ ዲሬክተር የሚያስፈልገውን ሁሉ የሚያሟላ፥ ዲሬክተር ደግሞ የትምህርቱን አሰጣጥ ሒደት የሚመራ ነው። በደንቡ ውስጥ የሁለቱ የሥራ ድርሻና የኃላፊነት ልክና ገደብ በሃምሳ ሦስት አንቀጾች በግልጽ የሰፈረ ነበር። ይኸ እነሱ በሌሎች ሲተኩም የጸና ደንብ ነበር።[16]

ስለዚህ፥ ትምህርት ቤት ሲዘጋ ቲያትር ይቀርብ የነበረው በውጭ ቋንቋ ሆኖ ሳለ፥ ባንዱ ፋንታ በአማርኛ ይቅረብ ለማለት ውሳኔው የትምህርት ሚኒስቴር ነበር። በመሆኑም፥ የአምስተኛ ክፍል ተማሪ የነበረው ሐዲስ ዓለማየሁ፥ ትምህርት ቤት በ1923 ሐምሌ ሲዘጋ እንዲታይለት ከዚያ ቀደም ብሎ "ያበሻና የወደኋላ ጋብቻ"ን ተውኔት ከጻፈ በኋላ፥ ማሳየት እንዲቻል እንዲፈቀድለት ወደ የትምህርትና የጥበብ ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር ወደ አቶ ሣህሌ ፀዳሉ መሔድ ነበረበት።

አቶ ሣህሌ ፀዳሉም፥ ቲያትሩን (ጽሑፉን) ከተመለከቱት በኋላ፥ "ትምህርት ቤት በሚዘጋበት ጊዜ የውጭ አገር ዲፕሎማቶችና ሌሎች ፈረንጆች ስለሚገኙ፥ በማያውቁት ቋንቋ እንደዚህ ያለ ረዥም ቲያትር ማሳየት አይገባም" ብለው በመወሰናቸው ሳይታይ ይቀራል።[17]

ሆኖም፥ በሁለቱ የውጭ ቋንቋዎች ቲያትሮቹ ሲቀርቡ ታዳሚዎቹ፥ ባለሥልጣኑ ከጠቀሷቸው ሌላ፥ ባብዛኛው እነኚያን ቋንቋዎች የማይሰሙ ኢትዮጵያውያን ወላጆችና እንግዶች እንደ ነበሩ በማሰብና፥ ቲያትሩም እንዳይታይ በመከልከሉ፥ ውሳኔው ወጣቱን ሐዲስ ዓለማየሁን ሳያሳዝንና ሳያስቆጣ አልቀረም ነበር። ውሳኔው ግን ጸና።

የ1923 የትምህርት ዓመት ሲፈጸምና በትምህርት ብልጫ ላገኙ ተማሪዎች ሽልማት ሲሰጥ ሐዲስ ዓለማየሁ ከአምስተኛ ክፍል (በእንግሊዝኛው ዘርፍ) ሁለተኛ ወጥቶ ሰኔ 27 ቀን ሽልማት ያገኛል። ሆኖም፥ ቀደም ሲል ባንዳንድ መምህራን ላይ የነበረው ቅሬታ ወደ አድማ ተቀይሮ ረብሻ እስከ ማስነሣት ደርሶ ስለነበረ፥ ሽልማቱ ከዚያ ለተከተለው ብርቱ ቅጣት መዳኛ አልሆነም። እንደ ሐዲስ ዕድሜያቸው 18 ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆነ (ሐዲስ 21ኛ ዓመቱ ላይ ነው)፥ "በነዋሪነት (ባዳሪነት)" ሳይሆን በተመላላሽነት እንዲማሩ ይወሰንባቸዋል። በዚያን ወቅት እዚያው ተማሪ የነበሩት ክቡር አቶ አማኑኤል አብርሃምም ሁኔታውን በምሬት ገልጸውታል፤ ". . . መልካም ውጤት ያስገኘሁትን ወጣትና እንደ እኔ ለአያሌ ዓመታት በትምህርት ገበታ ላይ የቆዩትን ሠላሳ የሚያህሉ ጓደኞቼን፥ የክረምት ወራት መሆኑን እያወቁ፥ ለስንቅ አንድ ብር እንኳን ሳይሰጡን፥ የትምህርት ቤቱ በተዘጋ ማግሥት ሚኒስትሩ በድንገት አባረሩን . . . በሚኒስትሩ ትእዛዝ በዚያው ዕለት ከትምህርት ቤቱ መውጣት ግዴታ ስለነበረ . . . ."[18]

እዚህ ላይ ለመባረሩ ምክንያት የሆነው ነገር አልተገለጸም። ይሁን እንጂ፥ ክቡር ዶክተር ሐዲስ ዓለማየሁ *ትዝታ* በተሰኘው መጽሐፋቸው (1985) በሚከተለው አኳኋን ገልጸውታል።

> . . . በጊዜው ይሰጥ የነበረው ትምህርት አጥጋቢ ካለመሆኑም ሌላ፥ አንዳንድ አስተማሪዎች ችሎታ ያልነበራቸው በመሆናቸው እንዲለወጡ፥ ችሎታ ካላቸው መካከልም አንዳንዶቹ የስካር አመል ስለነበራቸው በትምህርት ጊዜ ሰክረው እቤታቸው የሚውሉ በመሆናቸው አቤቱታቸውን ደጋግመው አሰምተው ምንም ስላልተደረገላቸው፥ በፈተና ጊዜ አድማ አድርገው 'እንፈተንም' አሉ።[19]

ይህ ውሳኔ (ተመላላሽ ሆነው እንዲማሩ የሚለው)፥ በአዲስ አበባ ዘመድ ለሌላቸው ከትምህርት ቤት ይውጡ የማለት ያህል ነበር። በእርግጥ ውጤቱም ያ ነው የሆነው። ሐዲስ ዓለማየሁና አንዳንድ ጓደኞቹ የመጨረሻው ክፍላቸውን አቋርጠው ይወጣሉ።

ይህ 'ለምን እንዲህ ይደረጋል ወይም አይሆንም?' የሚል አቋሙ ለወጣቱ ትምህርቱን ከማቋረጥ የባሰ መስዋዕትም ያስከፈለው ይመስላል። ምክንያቱም፥ ከላይ በጠቀስነው በቄስ ባድማ *የብርሃንና ሰላም* (7ኛ ዓመት፥ ቁጥር 42) ጽሑፍ ውስጥ፥ በክቡር ቀኛዝማች ይመር አማካይነት በግዕዝ ተማሪ ቤት የተማሩ ስድስት ልጆች ልዑል ራስ ኃይሉ እየከፈሉ ". . . ሦስት ዓመት ያህል በተፈሪ መኮንን ተማሪ ቤት ሲማሩ ቆይተው ከፍ ያለ ትምህርት እንዲያገኙ መስከረም 28 ቀን 1923 ዓ.ም ወደ ቤይሩት ሰደዷቸው" ተብሏል። በ1920 በራስ ኃይሉ ከፋይነት ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ገብተው እስከ 1922 የትምህርት ዓመት መጨረሻ፥ ሦስት የትምህርት ዓመት የተማሩ ሐዲስና ጓደኞቹ እንደነበሩ ግልጽ ነው። ሔዱ ሲባል አምስቱ ብቻ መሆናቸው ባይጠቀስም፥ ሐዲስ በተፈሪ መኮንን አራተኛ ዓመቱን በ1923 መቀጠሉንና በዓመቱ መጨረሻ ከ5ኛ ክፍል የሁለተኝት ሽልማት ማግኘቱን ከዚህ በላይ ተመልክተናል። ከዚህም ሌላ፥ *ትዝታ* በተሰኘው መጽሐፍ፥ በገፅ 199 ላይ ይኸንን የሚያረጋግጥ ይገኛል። እነሆ፣

> አባቴ ቄስ ባድማና እኔ ከፖለቲካ ጽሕፈት ቤት ወደሳቸው ቤት እንደ ተመለስን፥ አቶ 'ብርሃኑ ወንድም' እና አቶ 'መኮንን ቸኮል' የኔን ወሬ ሰምተው መጡ። ከሁለቱም ጋር፥ ለከፍተኛ ትምህርት ወደ 'ቤይሩት' እስኪሄዱ ድረስ፥ ከሚሲዮን ትምህርት ቤት እስከ ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ድረስ አብረን ስንማር የኖርን ጉዋደኞች ነበርን። ከቤይሩት ሲመለሱ፥ እኔ ጎጃም በሥራ ላይ የነበርሁ በመሆኔ፥ ገና ያንለት መገናኘታችን ነበረ።

ስለዚህ፥ ሐዲስ ከጓደኞቹ ተነጥሎ መቅረቱ ብቻ ሳይሆን፥ ከመጨረሻ ክፍል ትምህርቱም የሚያጨናግፍ፥ አስገዳጅ ምክንያት ይፈጠራል። በመሆኑም ሐዲስ ገና በወጣትነት (21 ዓመት ማገባደጃው አካባቢ) ወደ ሥራው ዓለም እንዲያተኩር ይሆናል።

ከተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ከወጡት መካከል የተወሰኑና የሚግባቡት በድብቅ እየተሰበሰቡ ተመካክረው ህቡዕ ማህበር ስለማቋቋማቸው፥ አረጋዊው ሐዲስ በጻፉት *ትዝታ* በተባለው መጽሐፋቸው ውስጥ ተገልጾአል። ". . .ሁለት ወይም ሶስት ጊዜ ያክል በድብቅ እየተሰበሰብን ከተመካከርን በኋላ፥ ማህበር እንድናቋቁም ወሰንን . . ."[20] የማህበሩ ዓላማም የኢትዮጵያን ልማት ማፋጠን

ነበር፡፡ ሐዲስን ሰብሳቢ አድርገው ይመርጣሉ፡፡ ለማህበሩ የገንዘብ ምንጭ እንዲሆኑ ከታሰቡት አንዱ ቲያትር ማሳየት ነበር፡፡

በዚህም መሠረት፥ የመጀመሪያው ቲያትር ቀደም ብሎ ለተፈሪ መኮንን የትምህርት ቤት መዝጊያ ቀን እንዲቀርብ ታስቦ በሐዲስ የተጻፈው "ያበሻና የወደኋላ ጋብቻ" የተሰኘው ተውኔት ሆኖ እንዲቀርብ አባላቱ ይስማማሉ፡፡ ከላይ እንደጠቀስነው፥ ተውኔቱ በትምህርት ቤቱ መዝጊያ ቀን ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት አዳራሽ እንዳይቀርብ ተከልክሏል፡፡ ያኔ የተሰጠው ምክንያት መዝጊያ በዓሉ ላይ ቋንቋውን የማያውቁ ብዙ የውጭ ዜጎች መገኘታቸውና የተውኔቱ ረዥም መሆን ነበር፡፡ ስለ ተውኔቱ ይዘት፥ አቶ ሣህሌ ፀዳሉ "ጥሩ፥ መጥፎ"፥ ስለ ማለታቸው አልተገለጸም፡፡ ሆኖም፥ እሳቸው የትምህርትና የጥበብ ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር ቢሆኑም፥ ከበላይ ያለ ተቆጣጣሪያቸው ሚኒስትር ሳይሆን፥ ተጠሪነታቸው እንደ ሚኒስትር በቀጥታ ለዐፄ ኃይለ ሥላሴ ቀዳማዊ ስለ ነበረ የከለከሉትን "ይታይ" ብሎ መፍቀድ የሚችል 'ከጃንሆይ ሌላ የለም' ተባለ፡፡ ጉዳዩን እጃንሆይ ዘንድ የሚያደርስ፥ በትምህርት ሚኒስቴሩ ዋና ዲሬክተር ቅያሜ የማይሰጋ ሰው ሲያጠያይቁ፥ ያገር ግዛት ሚኒስትር የነበሩት ደጃዝማች ወልደ ጻድቅ ናቸው ይባላሉ፡፡ ስለዚህ፥ "የህቡዕ" ማህበሩ ሊቀ መንበርና ጸሐፊ (ሐዲስና ክብረ አብ ቢያድግልኝ) ወደኒሁ ሹም ይሔዳሉ፡፡

ትዝታ በተሰኘው መጽሐፋቸው ውስጥም፥ ጉዳዩን እግረ መንገዳቸውን አንሥተው እንዳተቱት፥ ሚኒስትሩ ተውኔቱን በንባብ አድምጠው ስለወደዱት ወጣቶቹን አመስግነው፥ ከትምህርት ቤት ውጭ እንዲታይ ከንጉሠ ነገሥቱ ፈቃድ ማስገኘት ብቻ ሳይሆን መሳፍንቱና መኳንንቱ እንዲያዩ ያሳዝዛሉ፡፡ ባገር ግዛት ሚኒስትሩ ቀላጤነትም የ15 ዓመት ወጣት ከነበሩት ከአልጋ ወራሹ ጀምሮ፥ መሳፍንቱ፥ መኳንንቱና ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣኖች እንዲታደሙ ይነገርላቸዋል፡፡ የሚታየው ሆቴል በመሆኑ ንጉሠ ነገሥቱ እዚያ ሊገኙ አይችሉም ነበረና፥ በሌሎቹ ፊት ቲያትሩ ጳጉሜ 1 ቀን፥ 1923 ታየ፡፡ ከቲኬት ሽያጭና ከታላላቅ ታዳሚዎች ርዳታ በርከት ያለ ገንዘብ ተገኘ፡፡ በድጋሚ ጥር 8 ቀን፥ 1924 ታይቶ፥ ከወጪ ቀሪ ከሰባት ሺ ብር በላይ ከሁለት ጊዜው ትርኢት ተገኝቶ በገንዘብ ያገኘው፥ በተወልደ ብርሃን የባንክ ሒሳብ ተከፍቶ ገቢ ተደረገ፡፡

ብርሃንና ሰላም የሚባለው ጋዜጣ በዘገበው መሠረት፥ ጳጉሜ 1 ቀን፥ 1923 (እሁድ) ቲያትሩ ሲታይ መክፈቻ ቃል ያነበበው ገብረአብ ቢያድግልኝ የተባለው ወጣት ሲሆን፥ ጥር 8 ቀን፥ 1924 ለሁለተኛ ጊዜ ሲቀርብ ደግሞ ሐዲስ ዓለማየሁ ነበር፡፡ ከሐዲስ የጥር 8 ቀን፥ 1924 ንግግር ውስጥ፥ ". . . [በዓለም] በድንቁርናው ዘመን፥ የገነነችና የሠለጠነች የነበረችው ሀገራችን አሁን

የዚያን ጊዜ ስማቸው ያልተጠራና የት እንደነበሩ ያልታወቁ ሀገሮች ሁሉ ሠልጥነው ራሳቸውን ችለው በተቀመጡበት ጊዜ እስዋ ወደኋላ ቀርታ" ትገኛለች የሚል ኃይለ ቃል ነበረበት። የገንዘብ እርዳታ ካደረጉት መካከል፥ ጎልተው የሚገኙት ፊታውራሪ ብሩ ሲሆኑ፥ ሁለቱም ተገኝተው በድምሩ 150 ጥሬ ብር ለግሰዋል። የሚገርመው ከልዑላኑ አንዱም ስሙ በዚህ አለመጠቀሱ ነው። ቲያትሩን ግን ከንጉሠ ነገሥቱ በቀር ያላየ አንድም ያገሪቱ ከፍተኛ ባለሥልጣንና ባለማዕረግ አልነበረም ማለት ይቻላል።[21]

ቲያትሩ የታየበት ቤት፥ "ሆቴል ማገኒስቲክ" የነበረበትን ትክክለኛ አድራሻ ማረጋገጥ የተቻለ ባይሆንም፥ የተለያዩ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት፥ ዛሬ 40 ፎቅ ይሠራበታል ተብሎ ተከልሎ ከታጠረው ቦታ፥ ወደ ዳግማዊ ምኒልክ አደባባይ አቅራቢያ በስተቀኝ በኩል ካለው አካባቢ ይመስላል የነበረው።[22]

ቲያትሩ የታየው በዚህ ሆቴል ሰፊ አዳራሽ የነበረ ሲሆን፥ ከተጠሩት ታላላቅ እንግዶች በተጨማሪ፥ ቲኬት ገዝተው የገቡም ስለነበሩ፥ ቦታው እስከ መጨናነቅ ደርሶ እንደ ነበረ ጸሐፊ ተውኔቱ ያስታውሳሉ። በተለይ በመክፈቻው መዝሙር፥ "ተነሥ ታጠቁ" (ለሥራ፥ ለሀገር ልማት - ያኔ የፋሽስት ወረራ ጨርሶ አልታሰበም ነበርና) በተሰኘው ውስጥ፥ የሚንጸባረቀው ያገር ፍቅር ስሜት ቀስቃሽ ስለነበረ የተመልካችን መንፈስ አነሣሥቶ ነበር። ድጋሚ ለመታየት ያበቃውም የዚህ መንፈስ ግፊት አለመብረድ ይመስላል። የሆቴሉም አመራር መጀመሪያ የጠየቀውን የአዳራሽ ኪራይ ለሁለተኛው ጊዜ ሳይጠይቅ ለወጣቶቹ አዳራሽ በነጻ ፈቀደላቸው። ከትልልቅ ወጪዎቻቸው ዋናው የሆቴሉ ኪራይ (80 ብር) ስለ ነበር፥ የሆቴሉ ባለቤት የነበሩት ግሪክ (ሙሴ ፓፓታኪስ?) ያደረጉት ቀላል አስተዋጽኦ አልነበረም። ከሌላ አንፃር ግን፥ ሆቴሉም ካላስከፈለው 80 ብር የበለጠ ጥቅም ያገኘ መሆኑ ገሀድ ነው! ከሀገሪቱ አልጋ ወራሽ ጀምሮ ልዑላን መሳፍንትና መኳንንት ሁሉ ያቺን ሆቴል ለማየት ሲሉ አንዳቸውም ይሔዱ እንዳልነበር እሙን ነው። ስለዚህ፥ ባለሆቴሉ ይኸን ክብር ላስገኘለት ቲያትርና አዘጋጆች ከፍተኛ የውለታ ባለ እዳ መሆኑ ግልጽ ነው።

ከዚህ ቲያትር ድጋሚ መታየት በኋላ ምን እንደ ተከተለ ከደራሲው ብዕር እናንብ፤

> . . . ከዚያ ወዲያስ? ከዚያ ወዲያማ ምንም ያክል ጊዜ አዲስ አበባ ሳንቆይ፥ በሥራ ወደየጠቅላይ ግዛቱ እንድንበታተን ተደረገ! ላገራችን ዕድገት የታሰበው ብርም፥ ባንክ እንደ ተቀመጠ፥ ነፃነትዋን ሊያጠፉ ለመጡት ፋሽስቶች ሆነ!

> . . . አሳባችን የልጆች አሳብ እንደመሆኑ፥ በህልም ተራ እንደሆነ እንጂ፥ በዕድገት እቅድ ተራ ገብቶ የሚታይ አለመሆኑ መቼም የቅድንና ያፈፃፀሙን ስራ ለሚያውቁ ሁሉ ግልፅ ነው! ግን፥ ቢትወደድ ወልደ ጻድቅን ጎሬ ከማግኘቴ ጋር ከብላቴን ጌታ ኅሩይ ፀዳሉ ጋር በነበረን ፍልሚያ የዋሉልን ውለታ፥ ትዝታዎቻቸው እስከ ዛሬ ከሚያጫውቱኝ የልጅነት አሳቦቻችንና ትግሎቻችን አንዱ ነው::[23]

የ'ህቡዕ ማህበሩ'ና የሐዲስ "ያበሻና የወደኋላ ጋብቻ"፥ በአዳራሹ ጢም ላለ ታዳሚ ሁለት ጊዜ ታይቶ፥ ከፍ ያለ የመንፈስ መቀስቀስ ያስከተለ ስለመሆኑና በታዳሚ ዘንድም ስላሳደረው ውዴታ የሰሙት ንጉሠ ነገሥት (ኋላ ዘመን ሲያደርጉ ይስተዋል እንደ ነበረው) ቲያትሩ ቤተ መንግሥት (ግንቦት አንድ ቀን፥ 1924 የሚፈጸመውን የልጃቸውን፥ የልዑል አልጋ ወራሽ አስፋወሰንንና የልዕልት ወለተ እሥራኤል ሥዩምን ሠርግ ምክንያት በማድረግ በነበረው ያንድ ሳምንት ያህል ዝግጅት ላይ) እንዲታይ ጠየቁ:: ሆኖም፥ ለሠርግ የሚሆን የሣቅ፥ የደስታና የፌንጠዝያ አፍላቂ ተውኔት እንጂ፥ እንደ "ያበሻና የወደኋላ ጋብቻ" የሚጎመዝዝ እውነታ ሥሎ የሚያስለቅስ ቲያትር የሚሆን አልነበረምና፥ ሌላ ቲያትር ሐዲስና ጓደኞቻቸው እንዲያዘጋጁ ተደረገ::

ዝግጅቱ በታላቁ ቤተ መንግሥት ሲቀርብ ግን ብቻውን እንዳልነበር የወቅቱ ጋዜጣ የዘገበውን እንጠቅሳለን፤

> . . . ግንቦት 8 ቀን [1924] ከ7 ሰዓት ጀምሮ እስከ ማታ ድረስ በታላቁ ቤተ መንግሥት፥ በዳግማዊ ምኒልክና በተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት የሚማሩ ተማሪዎች የሚያስደንቅ ትያትር አድርገው፥ ጃንሆይንና እቴጌን፥ መኳንንቱንና ወይዛዝሩን ሁሉ ደስ አሰኙ:: ትያትሩንም አዘጋጆች ለዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት አቶ ዮፍታሔ ንጉሤ ነው:: ለተፈሪ መኮንን ት/ቤት ሐዲስ ዓለምአየሁና ዘሪሁን ወግ አየሁ ናቸው. . . .(24)

(ይህን ሠርግ አስመልክቶ ሁለት ነጥቦች ልብ ይሏል:: 'ግንቦት የጋብቻ ወር አይደለም' የሚለው ምልኪ መጣሱንና፥ የአግቢው ልዑል ዕድሜ ገና 16 ዓመት እንኳ ያልሞላ የልጆች ዕድሜ የነበረ መሆኑን::) ይኼ የቲአትር ዝግጅት ለሐዲስ ከንጉሠ ነገሥቱ ሽልማት ማስገኘት ብቻ ሳይሆን፥ በቲያትርና በመዝሙር ድርሰት ሰፋ ባለ ታዳሚ ዘንድ ታዋቂነትን አተረፈላቸው::

ለዚህ ዋቢ፥ ፋሽስት ኢጣሊያ ከሀገራችን ከተባረረች በወራት ውስጥ የታተመውን፥ *ያዲስ ዘመን መዝሙር (ለነፃነት ክብር)*ን፥ እንጠቅሳለን:: የዚህን መጽሐፍ መቅድም የጻፉት (1933)፥ አቶ ይልማ ዴሬሣ ነበሩ:: መቅድሙ ብዙ

መሠረታዊ ጉዳዮችን የሚያነሣ ሲሆን፥ አሁን የምንጠቅሰው ከቲያትሩ ሐተታ ውስጥ አንዷን ነጥብ ነው፡፡ እነሆ፤

> . . . ከኢትዮጵያና ከኢጣልያ ጦርነት አስቀድሞ፥ በቲያትር ድርሰት ከፍ ያለ ጥበብ ለማሳየትና ብዙ የሥልጣኔ እርምጃ ለማመልከት፥ ባለቲያትሮችና የቲያትር ሠራተኞቹ በሥራው ስለሠለጠኑበት፥ ዘመኑ አዲስ ዘመን ሆኖ ነበር. . . . ከነአቶ ዮፍታሔ ንጉሤ፥ ከነሐዲስ ዓለማየሁ፥ ከነአቶ መላኩ በጎሰው፥ ከሌሎቹም ብልሆች ሁሉ ተደርሰው የነበሩት የቲያትር 'መጽሐፎች' (?) ሥራቸውም ምስጢራቸውም ብዙ ዐይነት መንገድ ያመለክት ነበር. . . .[25]

(ጥቅሱ 'የቲያትር መጽሐፎች' የሚለው ዛሬ 'ቃለ ተውኔት' የሚሰኘውን ወይም ጽሑፉን ለማለት እንጂ በዚያን ጊዜ ከነዚህ ቲያትሮች ውስጥ ከበጅሮንድ ተክለ ሐዋርያት "የአውሬዎች ኮሜዲያ" (ከፋቡላ ጋር) በስተቀር በመጽሐፍ ቅጽ የታተመ ስለመኖሩ መረጃው ያጠጠ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ሁኔታው ዛሬም ያው ነው፡፡)

ከዚህ ጥቅስ የምንገነዘበው፥ ክቡር ዶክተር ሐዲስ ዓለማየሁ በቲያትሩ መድረክ ላይ ብቅ ባሉባት አጭር ጊዜ (1922-1924)፥ በዘመነኞቻቸው ዘንድ በዚህ ዘርፍ ስላላቸው ሁነኛ ሥፍራ እና፥ አሻራቸውን አሳርፈውበት እንደ ነበረ ነው፡፡ ይህ ቃል በ*ያዲስ ዘመን መዝሙር መቅድም* ውስጥ በ1933 ታትሞ ሲወጣ ሐዲስ በግዞት ገና ኢጣሊያ እንደነበሩም ልብ ይሏል፡፡

ስዊድን ሚሲዮን፥ ሐዲስ ትምህርታቸውን ሲጀምሩበት፥ ዛሬ መካነ የሱስ ቤተ ክርስቲያን እተተከለበት ስፍራ ነበር፡፡ ሐዲስ የመምህርነት ሥራቸውን በጀመሩበት ጊዜ ግን፥ እንጦጦ መንገድ ላይ፥ ዛሬ ዩኤስ ኤምባሲ ከሚገኝበት ጎን ከበስተእንጦጦ በኩል ነበር፡፡ እዚያ እያስተማሩ ሳሉ፥ ነጋድራስ ወዳጆ ዓሊ የጎጃም ነጋድራስ ነበሩ፡፡ በዚያን ጊዜ የእንግሊዝ ቆንስላ በዳንግላ (አገው ምድር) "ከተማ" ተከፍቶ ነበር፡፡ ነጋድራሱ እዚያ ለነበረው የጉምሩክ መሥሪያ ቤት የተማሩና ሁነኛ ሰዎች ፈልጉልኝ ሲሉ፥ ሐዲስ ይጠቆማሉ፡፡ በሁለቱም ወገን ስምምነት ወደ ዳንግላ ጉምሩክ ይሔዳሉ፡፡

ሐዲስ በዳንግላ የነበራቸውን የጉምሩክ ተግባራቸውን እንደሚከተለው ይገልጻሉ፤

> . . . በጉምሩክ ውስጥ የተቆጣጣሪነት ሥራ ነበር የምሠራው፡፡ በተቆጣጣሪነቴ፥ በየወሩ መጨረሻ ሒሳብ በሚወራረድበት ጊዜ ካልሆነ ብዙ ሥራ አልነበረኝም፡፡ ስለዚህ አለቃዬ፥ ብላታ ኅለተ ወርቅ እሸቴ፥ ከጉምሩክ ሹምነታቸው ሌላ፥ 'የባርያ ነጻ' ሹም ጭምር ስለነበሩ፥ የሥራዬን ቀላልነት በመመልከት በ'ባርያ ነጻ' ክፍልም እንድረዳ ጠይቀውኝ፥ 'በወዶገባነት' ሊተባበሩኝ ከፈቀዱ

> ጓዋደኞቼና እሳቸው ለዚያ ሥራ ከመደቡዋቸው ወታደሮች ጋር ባንድነት ሆነን እንሠራ ጀመር። ምንም እንኳዋ በባሪያ የሚነግዱ የተያዙ ሰዎች በስቅላት እንደሚቀጡ ቀደም ብሎ የታወጀ ዐዋጅ ቢኖርም፥ በዚያ ጊዜ፥ ብርቱ የባሪያ ንግድ በምስጢር ይካሄድ ስለነበረ፥ ሥራችን 'ባሪያ ፈንጋዮችን'ና በጠቅላላው ባሪያ ነጋዴዎችን እያደኑ የያዙዋቸውን ባሮች ነፃ ማድረግ ስለነበረ፥ ብዙ ባሮች ነፃ አደረግን።[26]

የዳንግላው የእንግሊዝ ቆንሲል፥ ሜጀር አር. ኢ. ቼዝማን የሚባል ነበር። በዚያን አካባቢ የእንግሊዝ ዜጎች ወይም በተለይ "የእንግሊዝ ጥቅም" የሚባል በሌለበት አካባቢ ቆንስላ ለምን እንደ ከፈቱ ማስገረሙ ወይም ጥያቄ ማሳደሩ አይቀርም። ላጭር ጊዜ በቆንስላው ጸሐፊነት የሠሩት፥ አቶ (ገብረ) ሕይወት ኀዳሩ፥ በዚያን ወቅት ስለታዘቡት፥ *ያቺም ቀን ተረሳች* (1967) በሚለው መጽሐፋቸው ጠቅሰውታል። ". . . ወደ ዳንግላ በተመለስን ጊዜ፥ በበጌምድር የሚቀመጡ ሚስዮናውያን መጥተው ነበርና፥ አንድ ቀን እኔ ባለሁበት ከቆንሲሉ ጋር ሲነጋገሩ፥ ቆንሲሉ ለዕረፍት ወደ ሀገራቸው የሚሔዱበት ጊዜ መድረሱን ቢናገሩ፥ ከሚሲዮናኑ አንዱ፥ 'ቢሔዱም እስኪመለሱ ድረስ በዚህ ክፍለ ሀገር የሚሆነውን ሁሉ በመከታተል እንጽፍልዎታለን' ቢሏቸው ገረመኝ. . . . በቆንሲሉ ሥራ ሲገርመኝ፥ በተጨማሪ የሚሲዮናዊውን ንግግር በሰማሁ ጊዜ፥ በልዩ ልዩ ስም ምን ዐይነት ሕዝብ በሀገራችን ውስጥ በመሀከላችን እንደተሠማሩብን ዐወቅሁ።" ቆንሲሉ በየሔዱበት ሁሉ "ሀገሩን ካርታ" ያነሣሉ፥ "ማናቸውንም ያዩትን ነገር በመከታተል እያጣሩ" ይጽፋሉ።[27]

በነገራችን ላይ፥ የሕይወትና በዳንግላ የተወለደው የሐዲስ ትውውቅና ወዳጅነት አቶ ሕይወት እስካረፉበት ጊዜ ድረስ የጸና ነበር።

ሜጀር አር. ቼዝማን፥ ኋላ፥ *የጣና ሐይቅና ጥቁሩ (ሰማያዊው) አባይ* በሚል ርእስ መጽሐፍ ያሳተመ ስለሆነ፥ መረጃውን ሲሰበስብ የነበረው ለዚሁ ዝግጅት ይሆናል ሊያሰኝ ይችል ይሆናል። ሆኖም፥ በዳንግላና በዚያ አካባቢ በስፋት የባሪያ ንግድ ከመኖሩ በተጨማሪ፥ የፋሽስት ኢጣሊያ መላ ኢትዮጵያን ወርሮ ቅኝ ግዛት የማድረጉን ሕልም ወደ ተግባር መለወጥ የማይቀር የመሆኑ ግምት በእንግሊዞች ዘንድ ያልነበረ አይሆንም። የቆንሲሉ ተግባር ፈርጀ ብዙ የነበረ መሆኑም አያጠራጥርም።

ይኸን እንዳለ እንተወውና፥ ቼዝማን በ1926 ታህሣሥ መጨረሻ ላይ ከዓመት ዕረፍቱ ከእንግሊዝ አገር ዳንግላ ተመልሶ ጥቂት እንደሰነበተ፥ "ቆንስላውን ዘግተህ ወደ ሱዳን እንድትመለስ" ተብያለሁ ብሎ ጸሐፊውንና የቆንስላውን ሠራተኞች ያሰናብታል። ይሁን እንጂ፥ መደበኛ ሥራውን ሲሠራ ቆይቶ፥

ቆንስላውን የካቲት 26 ቀን፥ 1926 ዘግቶ ወደ መተማ ሔደ። "መጋቢት 10 ቀን መተማ" ደረሰ።

ሐዲስ በበኩላቸው ስለዚህ ጉዳይ፥ "ዳንግላ፥ የመጨረሻው የእንግሊዝ ቆንሲል የነበሩት፥ ሜጀር ቺዝማን፥ ከዚያ ለቅቀው ሲነሡና በሳቸው እግር ሌላ ቆንስል እንደማይተካ ሲታወቅ፥ ቆንስላው ትምህርት ቤት ሆኖ፥ እኔ ወደዚያ ተዛውሬ ትምህርት ቤቱን እንዳቋቁም"[28] ተደረገ ይላሉ። የትምህርት ዓመቱ ሐምሌ መጀመሪያ ላይ ይፈጸማል ብለን ብንገምት፥ ትምህርት ቤቱ በመጋቢት ሲከፈት (ትምህርት ሲጀምር) የቀረው ጊዜ አራት ወራት ያህል ነበር ማለት ነው። ያም ሆኖ ግን፥ ትምህርት ቤቱ ለክረምቱ ረዥም ዕረፍት ሲዘጋ፥ ተስፋን በሚያነቃቃና በደመቀ ሥነ ሥርዓት ነበር።

ሐዲስ የሥራ መሪና አስተማሪ፥ መዝሙር ደራሲም ሆነው በሙሉ እንቅስቃሴ ላይ እንዳሉ ነበር "የወል ወል ግጭት" በኅዳር 1927 የተፈጠረው። ይህ ለማይጨው ጦርነት የመጀመሪያ የሆነው ደወል ሲደወል፥ የሐዲስን የወደፊት ሕይወት ሒደትና አግጣጫ ምን ያህል የሚለውጠው መሆኑን ያኔ ማንም ሊተነብየው የሚችል አልነበረም።

ከአራት ወር በኋላ፥ መጋቢት 1927፥ እየተሟሟቀ ይሔድ ለነበረው ለዳንግላ ትምህርት ቤት አዲስ ሥራ መሪ ተመድቦ፥ ሐዲስ በተራ መምህርነት ወደ ደብረ ማርቆስ ተዛውረው አዲሱን ኃላፊነታቸውን በትጋት ሲወጡ፥ የኢትዮጵያና የኢጣሊያ ግጭት ምን ያህል ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰ እንደ ነበረ ይገነዘባሉ። ሆኖም፥ ያለም መንግሥታት ማህበር ስለነበረና፥ ፍትህ ደግሞ ለማንም እንኳ ሊታይ እንደሚችለው፥ በኢትዮጵያ ወገን ነው ተብሎ በሁሉም ዘንድ የታመነ ስለ ነበረ፥ ለ1927 ክረምት ትምህርት ቤቱ ሲዘጋ ወደ እንዶዳም ለመሔድ ሐዲስ ፈቃድ ይጠይቃሉ።

"ለጎጃም የትምህርት ክፍል አላፊ" የነበሩት፥ አቶ ወልደ ጊዮርጊስ ተድላ (ኋላ ፊታውራሪ)፥ "በተከታዩ ዓመት አዳዲስ ትምህርት ቤቶች በሚከፈቱባቸው አንዳንድ አውራጃዎች ለጊዜው ስለሚያስፈልጉት አስተማሪዎችና ሌሎች አስቸኳይ መሰናዶዎች" ተመካክሮ ለመወሰን እስከ ነሐሴ አጋማሽ ቆይተው እንዲሔዱ ይፈቅዱላቸዋል።

እንዶዳም ኪዳነ ምሕረት ሔደው፥ ከአያታቸው ከካህን ዓለሙ ሥዩምና ከእናታቸውና ከሁለት እህቶቻቸው ጋር ተገናኝተው ናፍቆታቸውንና ዕረፍታቸውን ሳይጨርሱ፥ አቶ ወልደ ጊዮርጊስ ተድላ፥ ሐዲስን "ቶሎ ተመልሰህ ና" የሚል መልእክት በመላክተኛ ይልኩባቸዋል።

ደብረ ማርቆስ ሲደርሱ፥ ከጣልያን ጋር ጦርነት የማይቀር መሆኑንና ሕዝቡንና መኳንንቱን በቲያትርና ባደባባይ ንግግር መቀስቀስና ለጦርነቱ ማነሣሣት ማስፈለጉን፥ ለዚህ ደግሞ ሐዲስ ዐይነተኛ ሚና መጫወት የሚችሉ መሆናቸውን እንደሚያምኑ አለቃቸው ይገልጹላቸዋል። ስለዚህ ውይይታቸው መቋጫ፥ ሐዲስ እንዲህ ይላሉ፤

> እውነትም አቶ ወልደ ጊዮርጊስ እንዳሉት፥ አዲስ አበባ ማጀስቲክ ሆቴል የታየው፥ 'ያበሻና የወደኋላ ጋብቻ' የተባለ ቲያትር የመጨረሻ ክፍል፥ ያጥራል እንጂ፥ በጊዜው ለተፈጠረው ሁኔታ የሚስማማ ሆኖ አገኘሁት. . . . ይህ የመጨረሻው ክፍል . . . በ'ወደሁዋላ' ፋንታ 'ፋሽስት ኢጣሊያ'ን ተክተን፥ እንዲስማማ ማሻሻያ ለውጦች ተደርገውለት፥ ለታሰበው ሥራ ሊሆን እንደሚችል ላቶ ወልደ ጊዮርጊስ ነገርሁዋቸው።[29]

ከዚህ በተጨማሪ፥ ሁለተኛና አጠር ያለ ቲያትር፥ ዐጽመ ታሪኩ ከዐድዋ ጦርነት መነሻና መደምደሚያ ጋር የሚመሳሰል ጽፈው፥ ሁለቱም ተባዝተው ለተዋናዮች ታድለው ቲያትሮቹ ከታሰበው ጊዜ ቀድመው ለመታየት በቅተዋል።

ስለዚህ የድርሰት ሥራቸው ዶክተር ሐዲስ ዓለማየሁ በ*ትዝታ* ውስጥ ሲገልጹ፥ "መቼም ያ በጥቂት ቀናት ውስጥ የተደረሰው ቲያትር፥ የሰውን ስሜት ቀስቅሶ ለማሸለልና ለማስፎከር ያክል የሚበቃ ከመሆን ዐልፎ በኪነት መልኩ ሲታይ፥ 'ከቲያትር ተራ ገብቶ የሚቆጠር ነበር' ለማለት አያስደፍርም" ይላሉ። 'ምነው ጽሑፎቹ ኖረው በነበረና ፍርዱ ለሌላ በተተወ ኖሮ!' ያሰኛናል።

ሐዲስ፥ ልዑል ራስ እምሩን ተከትለው፥ ስድስት ራሳቸውን ሆነው ወደ ጦርነቱ ግምባር 1928 መጀመሪያ ላይ ዘመቱ። የዚህ ዝርዝር ታሪክ የሐዲስ *ትዝታ* (1985) ዋና ይዘት ስለሆነ፥ መጽሐፉን ማንበቡና ከሐዲስ ዓለማየሁ የሕይወት ታሪክ የስምንቱን ዓመት ያህል በራሳቸው ብዕር ተዘርዝሮ ማግኘቱ የተሻለ ነውና እዚህ አንገባበትም።

ወደ ግምባር ሲዘምቱ ስለ ሆነ አንድ ነገር ማንሣት ግን እንፈቅዳለን። ይኸውም በራሳቸው ቃል የሚገለጽ ነው፤

> . . . ዘሪሁንና እኔ፥ ራስ ከጎሬ ከመነሣታቸው ጥቂት ቀናት ቀደም ብለን፥ 'ቡኖ ዋቤኮ' ውስጥ 'ዋቤኮ አቦ' ወደሚባል አገር ሔድን። ዋቤኮ አቦ አባቴ ካገራቸው ከጎጃም ሄደው ረዥም ጊዜ ይኖሩበት የነበረ፥ ከወለጋ መንገድ ምንም ያክል የማይርቅ አገር ነው። ስለዚህ፥ አባቴን አይቼ ወዲያውም በቅሎችና በቂ ስንቅ ስላልነበሩኝ፥ በዚያ አጭር ጊዜ ሊገኝ የተቻለውን ያክል ይዘን፥ ራስ በዚያ ሲያልፉ እንደምንገናኝ ዐውቀን ነበር የሔድን።

> አንድ ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ፥ ራስ እኛ ወደ ነበርንበት አገር መቅረባቸውን ስለ ሰማን፥ አባቴ የሰጡኝን ሁለት በቅሎዎችና ስንቅ ይዘን እሳቸው [አለቃ ዓለማየሁ ሰሎሞን] ጭምር 'ሱጴ' እስከምትባል አገር ድረስ አብረን ሔደን ከራስ ጋር ተገናኘን።
>
> "ልጅዎ ያለሥራው ከወታደር ጋር ዘማች ሆኖ እንደሚያዩት ካገር አገር ይዞራል። አሁን በደህና ከርስዎ ጋር አገናኝተነዋል፥ ከእንግዲህ መክረው ከርስዎ ጋር እንዲቀር ያድርጉት" አሉዋቸው ራስ፥ አባቴን ተቀብለው ሲያነጋግሩዋቸው። ከልባቸው ይሁን ወይም የሚሉትን ለመስማት እንደሆነ አላውቅም። 'እንኩዋንስ እሱን ከኔ ጋር እንዲቀር ልመክረው፥ ባልሸመግል ኖሮ እኔም አብሬዎ ብሔድ በወደድሁ ነበር'[!] አሉ አባቴ።[30]

ከዚህ ጥቅስ ከምንገነዘባቸው ነገሮች አንዱ፥ ምንም አባታቸው ከጎጃም ወደ ጎሬ በመጡ ጊዜ ሐዲስ ገና ሕፃን የነበሩና፥ የልጅነትና የወጣትነት ኑሮዋቸው ጉዞ ከላይ የጠቀስነው ቢሆንም፥ ካባታቸው ጋር ያልተቋረጠ ግንኙነት የነበረ መሆኑን ነው። በዚህ ወቅት ሲገናኙ ሐዲስ የ27 ዓመት ባለዕድሜ ለመሆን እየተቃረቡ ነበር። ልዑል ራስ እምሩም ያኔ 45 ዓመት ግድም ስለነበሩ፥ ዓለማየሁ ሰሎሞን "ባልሸመግል ኖሮ" ሲሉ፥ በግልጽ የሚታይ የዕድሜ ብልጫ ነበራቸው ማለት ነው። 'ያኔ ምናልባት ወደ ስድሳው መጨረሻ ወይም ወደ ሰባው መጀመሪያ ይሆኑ ነበር ይሆን?' ያሰኛል።

ይሁንና፥ ሐዲስ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣን በነበሩበት ጊዜ ሁለቱንም ወላጆቻቸውን አዲስ አበባ አምጥተው በዛሬው መኖሪያ ቤታቸው መጠራቸውን፥ በቃለ ምልልስ በተደገፈው "የአርትስ ባችለር ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉ ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት" ባቀረበችው ጽሑፍ ውስጥ ፊለቀች እሸቴ አስፍራለች።[31]

ከትዝታ ትረካ ጎልቶ የሚወጣ አንድ ቁም ነገር አለ። ይኸውም፥ በዚያ በቀውጢ ቀን ገና በአወቋቸው፥ በልዑል ራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴ ዘንድ፥ ወጣቱ ሐዲስ ዓለማየሁ ከፍተኛ ግምት የተሰጣቸው የነበሩ መሆኑን ከጦርነቱ ታሪክ ሒደት እንገነዘባለን። ለአርበኛው የሚያስፈልገውን ነገር ከሱዳን ገዝተው፥ ኋላ ከሚነገራቸው ቦታ ድረስ ይዘው እንዲመጡ፥ ከዚያው ከጦሩ ግንባር መልስ፥ ታምነውና፥ ያሳካሉ ተብሎ ታምኖባቸው፥ ከዚያ ሁሉ ሰው መካከል ተመርጠው፥ ያን ያክል ገንዘብ፥ ጳጳስ እንኳ በሚከዳበት ጊዜ ይዘው ወደ ውጭ አገር እንዲሔዱ መደረጉ፥ ለሰብእናቸው የነበረውን ትልቅ ግምት የሚያረጋግጥ ይመስለናል። የልዑል ራስ እምሩን ሰው የመመዘን ችሎታም ያሳያል።

በግንባርም፥ በአርበኝነት የተደረገው ጥረትም ሳይሳካ ቀርቶ በጥር ወር መጨረሻ 1929፥ ሐዲስ ዓለማየሁ ከአቶ ይልማ ዴሬሣ ጋር ወደ ኢጣሊያ በግዞት ተላኩ። በዚያ ስላጋጠማቸው ነገር ሁሉ የጻፉት ስለሆነ *ትዝታ* የሚለው መጽሐፋቸውን ማንበብ ይቻላል።

ቀደም ብሎ ልዑል ራስ እምሩም ተመሳሳይ ዕጣ የደረሳቸው መሆኑንም ልብ ይሏል። በግዞትም አብረው ነበሩ። ሁለቱም ኢጣልያ ከሀገራችን ተባርራ ከወጣችና የሙሶሎኒ መንግሥት ከወደቀ በኋላ፥ ነጻ ሆነው ወደ ሀገራቸው በ1936 ከግዞት ይመለሳሉ። ከስድስት ዓመት በላይ ኢጣልያ በግዞት ቆይተው ማለት ነው። ልዑል ራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴ፥ መስከረም 20 ቀን 1936 አዲስ አበባ መግባታቸውን `የዘመኑ ሳምንታዊ ጋዜጣ፥ *ዘኢትዮጵያን ሔራልድ* የተሰኘው የእንግሊዝኛ ቋንቋ ጋዜጣ ሲዘግብ፥ የዚያን ጊዜ ሣምንታዊው *አዲስ ዘመን* ደግሞ፥ ቅዳሜ ኅዳር 17 ቀን፥ 1936 በወጣው ቁጥሩ (ቁ.30)፥ "የእሥረኞች መግባት" በሚል ርእስ ሥር አጭር ሐተታ አድርጎ፥ ሲደመድም፥ ". . . እነዚህ እሥረኞች በመንፈሳቸው ከጠላት ጋር በብርቱ የተከራከሩ የመንፈስ አርበኞች ናቸው" ይላል። ከዚያ፥ የአሥራ አምስት ሰዎች ስም ይዘረዝራል። ከነዚህ መካከል አንዱ ሐዲስ ዓለማየሁ ናቸው። አዲስ አበባ፥ የገቡባት ዕለት ቅዳሜ ኅዳር 10 ቀን 1936 ናት። አብረው ከመጡት መካከል፥ ስምንት አባላቱ በግዞት የኖሩ አንድ ቤተሰብ ነበር! እሱም ተወላጅነታቸው አርመን የሆነው ኢትዮጵያዊ፥ የሙሴ አብርሃም ኮራጅ[ያን] ቤተሰብ ነበር። ሙሴ አብርሃምና ባለቤታቸው ከስድስት ወንዶች ልጆቻቸው ጋር ነበር በኢጣልያ ተግዘው የቆዩት! ሙሴ አብርሃም ኋላ የጠቅላይ ግምጃ ቤት ሹም ሆነው ሠርተዋል።

ክቡር ዶክተር ሐዲስ ዓለማየሁ፥ ከግዞት እንደተመለሱ፥ መንግሥት ከጠላት ከተወረሱ ሕንፃዎች አንዱ ውስጥ ማረፊያ ሰጥቷቸው፥ ሥራም ያኔ በጽሕፈት ሚኒስቴር ሥር ይገኝ በነበረው የጋዜጣ ክፍል ተሰጣቸው። በዚህ ወቅት፥ በእንግሊዝኛ አንድ መጣጥፍ በ*ኢትዮጵያን ሔራልድ* ላይ አወጡ። ርእሱም፥ "ሰባት ዓመት በስደት" ወይም በእንግሊዝኛ "ሰቨን ይርስ ኦቭ ኤግዛይል" የሚል ነበር። በጋዜጣው ላይ የወጣው *ታህሣሥ* 1 ቀን፥ 1936 (11/12/43) ነበር።

በጋዜጣው ክፍል ሥራ እንደያዙ ለረዥም ጊዜ የተለዩዋቸውን ዘመዶቻቸውን ለመጠየቅ ጎጃም ሔደው ሲመለሱ፥ ለቅርብ አለቃቸው አንድ ሐሳብ ያቀርባሉ። ያን ሐሳብ ራሳቸው ለጃንሆይ እንዲያቀርቡ ይመክሯቸውና ይዘው ይቀርባሉ። በዚህ ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ፥ የገጠር እርስት፥ የከተማ ቦታና ቤት እንዲሰጣቸው እንዲጠይቁ ይነግሯቸዋል። ሐዲስ ግን ይኸን ለማድረግ የሚያበቃ አገልግሎት እንደሌላቸው እና ለመጠየቅ የሚቸገሩ መሆኑን ይገልጻሉ።

በጦር ግምባር ከመዋጋት፥ በአርበኝነት ከመታገልና በግዞት ከመማቀቅ በላይ ለሀገር ማገልገል ምን ሊኖር እንደሚችል ሲጠይቋቸው፥ "ይኽን ሁሉማ ያደረግሁት ለራሴ ነው። አገር ከጠፋ ምን ኑሮ አለ ብዬ። ለዚህ ደግሞ ሀገሬ ካሳ እንዴት ትክፈለኝ ብዬ እጠይቃለሁ?" የሚል መንፈስ ያለው መልስ ይሰጣሉ። ይኽን ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ ከት ከት ብለው ሥቀው በመደነቅ ዐይነት አስተውለዋቸው፥ "አንተ ገና ምኑም አልገባህ" ብለዋቸው ጉዳዩ ያከትማል።[32] እስከ 1936 መጨረሻ በዚህ በመጀመሪያ ሥራቸው ቆይተው፥ 1937 ላይ ወደ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ይዛወራሉ። ይህ ዝውውር የወደፊት የአገልግሎት መስካቸውን ወሳኝ ሆኖ ይገኛል። ምክንያቱም፥ ጥር 21 ቀን፥ 1961 ወደ "የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት" ተሾመው እስከገቡበት ጊዜ ድረስ በመንግሥት አስፈጻሚ አካል ውስጥ ተመድበው አስተዋጽኦ ያደረጉትና የቆዩት በአመዛኙ በውጭ ጉዳይ በኩል ነበርና ነው።

ውጭ ጉዳይ በተዛወሩ በሰባተኛው ወር መጨረሻ፥ መጋቢት 29 ቀን፥ 1937፥ "በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ቆንሲል" ሆነው ይሾማሉ።[33] በ1938፥ በኢየሩሳሌም ነዋሪ የነበሩትን ወይዘሮ ክበበ ፀሐይ በላይን አገቡ። ከኚህ የመጀመሪያም፥ የመጨረሻም ባለቤታቸው ጋር ለአሥራ አምስት ዓመታት ኖሩ። ግን ፍሬ ሳያገኙ፥ ወይዘሮ ክበበ ፀሐይ የጤና ማጣት ደጋግሞ አጥቅቷቸው በሞት ተለዩዋቸው (1953)።

ሐዲስ፥ በኢየሩሳሌም ሁለት ዓመት እንደ ቆዩ፥ በዩኤስ ይካሄድ በነበረው ዓለማቀፍ የቴሌኮሚዩኒኬሽን ጉባዔ ላይ እንዲሳተፉ ተልከው ኢትዮጵያን ወክለው ለአምስት ወር ይቆያሉ። የጉባዔው አጀንዳዎች ቴክኒካዊነት የሚያመዝንባቸው ስለነበሩ፥ ከሐዲስ መስክ ውጪ ቢሆኑም፥ ሁኔታው፥ ዲፕሎማት ለነበሩ ልዑካን እዚያው በዚያው እያጠኑ የመሳተፍ ጉዳይ ሆኖ ነበር።

ከጉባዔው ፍጻሜ በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ሥራቸው ሳይመለሱ በዚያው፥ ራስ እምሩ ኃይለሥላሴ በሚኒስትርነት በሚመሩት፥ "በዋሽንግተን የግርማዊነታቸው ሌጋሲዎን ዋና ጸሐፊ" ሆነው ነሐሴ 8 ቀን 1939 ተሾሙ።[34] በዚህ ሥራቸው ላይ በተደራቢ፥ በተባበሩት መንግሥታት "ትንሹ ጠቅላላ ጉባዔ" ተሳታፊ ይሆኑ ነበር። በዚች ጉባዔ ለመሳተፍ በየጊዜው ወደ ኒውዮርክ መመላለስ ነበረባቸው።

በዚህን ወቅት በጆርጅ ዋሽንግተን ዩኒቬርሲቲ በማታ ትምህርት ዓለማቀፍ ሕግ ማጥናት ጀመሩ።

መጀመሪያ አጋጥሟቸው የነበረው ችግር፥ ለምዝገባ መሟላት የሚገባቸውን የትምህርት ቤት ሰነዶች ማቅረብ የነበረ ቢሆንም፥ ያኔ በነበሩበት አቋም ገምግሞ ትምህርቱን ለመከታተል ብቃት እንደ ነበራቸው ለመወሰን አላስቸገረም ነበርና ችግሩ ውሎ አላደረም። በትምህርቱ ክትትል ላይ እንደ እንቅፋት የሚቆጠረው፥ በመደበኛ ሥራቸው ምክንያት ከዋሽንግተን ወደ ኒውዮርክ በየጊዜው እየተጠሩ ለስብሰባ መመላለስና ለተወሰነ ወቅት እዚያ ውሎ ማደሩ ነበር። ይኸም ቢሆን፥ በመጨረሻ የምስክር ወረቀቷን ከመውሰድ አናጠባቸው (አደናቀፋቸው) እንጂ፥ ዕውቀቱን ከመቅሰም አላገዳቸውም። እንዲያውም፥ ይህ ዓለማቀፍ ሕግ የሚባለው ከንድፈ ሐሳብ አልፎ በተግባር፥ ከመጻሕፍት ውጪ በተባበሩት መንግሥታት ሸንጎዎች ላይ ምን እንደሚመስል በገሀድ የሚያዩትና በትዝብት የሚገመግሙት ነበር!

የተባበሩት መንግሥታት 'ትንሿ ጠቅላላ ጉባዔ' ዘንድ የሚቀርቡት ጉዳዮች፥ በዓመት አንድ ጊዜ ወደ መስከረም ወር አካባቢ ለሚሰበሰበው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች (አንዳንዴም ርእሳነ ብሔር) ለሚሳተፉበት ጉባዔ የሚቀርቡ ዐይነት ነበሩ። 'በትንሿ ጉባዔ' ደረጃ (ማለትም በአምባሳደሮችና ሌላ ዲፕሎማቶች ደረጃ) ሊያልቁ የሚችሉትን ዓመት እንዳይጠብቁ ማድረጊያ የአሠራር ስልት ነበር። ስለዚህ፥ የኃያላንን ጥቅም በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ሲሆን የዓለማቀፍ ሕግ የሚባለው ምን ቦታ እንደሚሰጠው ከትምህርቱ ጋር ለማነጻጸር የማይገኝ ዕድል አግኝተው ነበረ። 'ንድፈሐሳብ ሌላ፥ ግብር ሌላ'።

ከሦስት ዓመት ከአምስት ወር በኋላ፥ ታህሣስ 10 ቀን፥ 1943፥ 'በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የክፍል ዋና ዲሬክተር'[35] ሆነው ወደ አዲስ አበባ ከዋሽንግተን ተሾመው ይመጡና፥ እስከ ሐምሌ ወር 1949 በሚኒስቴሩ ዋና መሥሪያ ቤት ሲያገለግሉ ይቆያሉ። ከስድስት ዓመት ተኩል በላይ መሆኑ ነው። ነገር ግን፥ ከግዞት ከተመለሱ በኋላ፥ ከሀገር ተመልሰው ወጥተው የዚያኑ ያህል ለመሆን ምንም ያህል ለማይቀረው ጊዜ በኢየሩሳሌምና በዩኤስ አሳልፈዋል። ስለዚህ፥ በግዞት ወደ ኢጣሊያ ከሔዱበት ጊዜ አንሥቶ እስከ 1949 ከነበረው ጊዜ ውስጥ ከግማሽ በላይ (60 በመቶውን) ያሳለፉት በውጭ ሀገር ነበር። ይህን ማንሣታችን ከጽሑፍ ሥራዎቻቸው ጋር ለማገናዘብ እንዲረዳ ነው።

ውጭ ጉዳይ ተመልሰው ከመጡ ዓመት ከሰባት ወር ያህል ከሆናቸው በኋላ፥ ሐምሌ 22 ቀን፥ 1944፥ 'በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ምክትል ሚኒስትር' ተብለው ተሾሙ።[36] ስለዚህ በዋናው መሥሪያ ቤት ከቆዩበት ስድስት ዓመት ያህል ጊዜ ወደ አምስት የሚጠጋውን በዚህ ከፍ ባለ የሥልጣን ደረጃ ነበር የቆዩት።

በዚሁ ወቅት፥ ሁለት መጻሕፍት በ1948 አሳተሙ። እነርሱም፥ *የትምህርትና የተማሪ ቤት ትርጉም እና ተረት ተረት የመሠረት* ናቸው።

እኚህ በወጣትነት ዕድሜያቸው መምህር የነበሩና የሀገራችንንም የዘመኑንም ትምህርት ከአጀማመሩ በተሳታፊነት ያስተዋሉ፥ የ46 ዓመት ጎልማሳ፥ ሁለቱም የትምህርት ሥርዓቶች ታላቅ ሕጸጽ እንዳላቸውና፥ በተለይ ዘመናዊ ተብሎ በፈጣን እርምጃ እንዲስፋፋ የሚፈለገው የትምህርት ሥርዓት በቅድሚያ ታርሞ ካልተስተካከለ፥ አደጋ ያለው መሆኑን ለማስጠንቀቅ የጻፉት ነበር ማለት ይቻላል። ዝርዝር ውስጥ ሳንገባ መሠረታዊ ሐሳባቸውን ከሚያንጸባርቁት ዐረፍተ ነገሮች ጥቂት እንመልከት።

> . . . ትምህርትና ተማሪ ቤት፥ ላንድ ማኅበር አቋም ዋና ዐምዶች ናቸው ማለት ይቻላል። ትምህርት የሚገኝበት ተማሪ ቤት ብቻ አለመሆኑን በዚች መጽሐፍ አመልክቻለሁ። ነገር ግን፥ በዘመናዊው ኑሮ ይብዛም ይነስ፥ በተማሪ ቤት ገብቶ ያልተማረ ሰው፥ ራሱንም ሆነ የሚኖርበትን ማኅበር እንደሚገባ ለማገልገል እንደማይችል የታወቀ ነው. . .።[37]

ይኼ፥ 'ትምህርት ቤት ገብቶ መማር' አስፈላጊነቱ የማያከራክር ስለመሆኑ፥ አቋማቸውን ግልጽ ያደረጉበት ነው።

ነገር ግን፥ በተማሪ ቤት ምን ዐይነት የተሟላ ትምህርት ያስፈልጋል? ሀገረኛውም ዘመነኛውም ተዋደው፥ ከሁለቱም ተወስዶ የተውጣጣ አዲስ ሥርዓተ ትምህርት ይፈጠር ነው ዋና መልእክቱ። ምክንያቱም፥ ". . . የኢትዮጵያ ጥንታዊ ትምህርት ቤቶች፥ ትምህርታቸውን በሃይማኖትና በኑሮ ሥርዓት ብቻ ወስነው፥ የኢኮኖሚን፥ ያስተዳደርን፥ የፖለቲካን፥ የወታደርነትን የተግባረ እድንና ሌሎችንም የጥበብ ትምህርቶች፥ ከትምህርት ሰሌዳቸው ውጭ ስለተዋቸው፥ በሰጡት ትምህርት የማኅበሩን ፍላጎት ሊያጠግቡ አልቻሉም። እንዲሁም፥ የኢትዮጵያ ዘመናውያን ትምህርት ቤቶች በጥበብ ትምህርት ብቻ ተወስነው፥ የማኅበራቸውን ታሪክ፥ የኑሮ ሥርዓት፥ ልማዱን፥ እንዲሁም ኢትዮጵያዊ አሰኝቶት የሚኖረውን ቅርስ፥ ከትምህርት ሰሌዳቸው ውጭ የተዉት እንደሆነ፥ ፍላጎቱ እንደሚገባ ይጠግባል ለማለት የሚያስደፍር አይመስለኝም።"[38]

ስለዚህ፥ የተሟላ ትምህርት የሚሰጡ ተቋማት ሊሆኑ የሚችሉት ከጥንቱም ከዘመናዊውም፥ የሰው ልጅን መንፈሳዊና ሥጋዊ ሕይወት ለማጥገብ የሚያስችሉትን ትምህርቶች አጣምረው የያዙት ብቻ ናቸው። እነሱን ዐይነቶቹ ከሌሉ የተሟላ ትምህርት የለም ነው ነጥቡ።

የሐዲስ ድምዳሜ ያገራችንን የዘመናዊ ትምህርት ተቋማት በሚመለከት ይኸ መሆኑን፥ ከሠላሳ ሁለት ዓመት በኋላ በታተመው፥ *የልምዣት* መቅድም ውስጥ በሚከተለው መልክ ቀርቦ እናገኘዋለን፤

> ይህን *የልምዣት*ንም ሆነ፥ *ፍቅር እስከ መቃብር*ንና *'ወንጀለኛው' ዳኛ*ን ለመጻፍ ሳስብ፥ ዐይነተኛ ዓላማ ያደረግሁት አንድ ነገር ነው። ጥንታዊው የኢትዮጵያ ሥራተ ማኅበር ማለት ያስተዳደሩ፥ የፍርዱ፥ የማኅበራዊ ኑሮና፥ እነዚህን የመሳሰለውን ሁሉ አጠቃልሎ የያዘው ጠቅላላ ሥራት፥ በዘመናዊው የትምህርት ድርጅት ውስጥ፥ በትምህርት መልክ ባለመሰጠቱ፥ መልካሙም ሆነ፥ ክፉው እየተረሳ በመሔድ ላይ ነው። ስለዚህ፥ . . . ዓላማዬ፥ ጥንታዊውን ሥራት ወይም ባህል በትምህርት ቤት በጥንቃቄ ተጠንቶና ተሙዋልቶ ሊሰጥ የሚችለውን ያክል ባይሆንም፥ በልብ ወለድ መልክ እንኩዋ፥ ከተከታይ ትውልዶች ጋር በመጠኑም ለማስተዋወቅ መሞከር ነው።[39]

ባጭሩ፥ ቀለል ባለና በተሟላ መልኩ በአስተዳደር መዋቅሩ ማስደረግ ካልተቻለ፥ በግለሰብ ደረጃ የበኩልን የመሞከር ነው፥ የልቦለዶቹ ሙከራ ግቡ።

*በተረት ተረት የመሠረት*፥ የተረት ድርሰቶች በዓለም ጥበበ ቃላት ውስጥ ከፍ ያለ ቦታ እንዳላቸው ሐዲስ ጠቁመው፥ ጊዜና ዐቅም ያላቸው፥ በሀገራችን በቃል የሚነገሩትን ሰብስበው እንዲያሳትሙ ጥሪ አቅርበው፥ ራሳቸው ደግሞ ከልቦናቸው አንቅተው ከጻፏቸው ዐሥራ ሁለት ተረቶች ውስጥ ዐሥራ አንዱን ለአንባቢያን ያበረክታሉ። ከነዚህ መካከል፥ በቅድመ ኅትመት ሳንሱር ያኔ ተከልክሎ የነበረው "አንበሳ ንጉሠ አራዊት"፥ ዐሥራ ስድስት ተረቶች ይዞ በ1985 እወጣው ሦስተኛ እትም ውስጥ ተካትቷል።

ሐምሌ 19 ቀን፥ 1949፥ "በተባበሩት መንግሥታት ማኅበር፥ በአምባሳደርነት ማዕረግ፥ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ዋና መልእክተኛ"[40] ተብለው ተሾሙ።

በዚህ ኃላፊነታቸው ወቅት፥ የተባበሩት መንግሥታት 'የኢኮኖሚ ኮሚሲዮን ለአፍሪቃ' (ዩ.ኤን.ኢ.ሲ.ኤ) የሚባለው አካል ዋና መሥሪያ ቤቱ በአዲስ አበባ እንዲቋቋም ቁልፍ ሚና ተጫወቱ። እንደሚታወቀው፥ የዚህ አካል አዲስ አበባ ላይ መሆን፥ የአፍሪቃ አንድነት ድርጅት ዋና ጽሕፈት ቤት አዲስ አበባ እንዲሆን በተደረገው ክርክር ውስጥ ተጨማሪ ድጋፍ ሆኖ ነበር። የሁለቱ እዚህ መኖር ደግሞ፥ ለሌሎች ዓለማቀፍ አካላትና ኤምባሲዎች መስህብ መሆኑ ብዙ የሚያከራክር አይመስለንም።

ተሳክቶ ቢሆን፥ የግል ታሪካቸውን እንዲጽፉ ይደረግባቸው ለነበረው ግፊት ተጨማሪ ኃይል ሆኖ፥ ሊያጽፋቸው ይችል ነበር የሚሉት፥ የሰው ልጅን በገፍ የሚያጠፉ መሣሪያዎችን ማምረት 'ዓለማቀፍ ወንጀል'፥ ፈብራኪዎቹንም 'ያለማቀፍ ወንጀለኞች' የሚያደርግ፥ ለተባበሩት መንግሥታት ሸንጎ አቅርበውት የነበረው የውሳኔ ሐሳብ ተቀባይነት ማግኘትና፥ በሱ ላይ ተመሥርቶ ዓለማቀፍ የቃልኪዳን ሰነድ መፈረም ነበር። የመጀመሪያው ዓላማ፥ ከብዙ መጓተትና መዘግየት በኋላ፥ የውሳኔ ሐሳቡ በቂ ድምፅ አግኝቶ እንደ ተባበሩት መንግሥታት ሐሳብ መግለጫ ቢደረግም፥ የቃል ኪዳን ስምምነቱ በምዕራባውያን ሀገሮች ብርቱ ተቃውሞና ሻጥር ሊፈረም እንዳይችል በመደረጉ፥ ሁለተኛውና ዐቢዩ ግብ ሳይደረስበት ቀረ። ያቋም መግለጫው 'የአስገዳጅነት' ኃይል የሌለው በመሆኑ ልፋታቸው በከንቱ እንደ ቀረ ቆጥረውታል። ይሁን እንጂ፥ እንደ አንድ አምባሳደር፥ ለዶክተር ሐዲስ ዓለማየሁ፥ ኃያል ለማትባል እንደ ኢትዮጵያ ላለች አንዲት ሀገር የተሞከረው ነገርና ውጤቱ ቀላል አይመስለንም።

በተባበሩት መንግሥታት የኃላፊነታቸው ወቅት፥ የኢትዮጵያን አጠቃላይ ምዕራብ-ደገፍ የውጭ ጉዳይ አዝማሚያም፥ በቀጥታ በፖሊሲ ደረጃ የመለወጥ ዐቅም ባይኖራቸውም፥ በተባበሩት መንግሥታት ኢትዮጵያን ወክለው በወሰዷቸው አቋሞች ወደ ማህል፥ ወደ ገለልተኛ፥ ባንዳንድ ጉዳዮችም "የግራ ፖለቲካ" አቋም ይሰኝ ወደነበረው አዝማሚያ ገፍተዋል።

ባንዳንዶቹ አቋሞቻቸው ሳቢያም፥ 'መመሪያ ሳትጠይቅ' በማለት ተጠይቀውባቸዋል። ለወቅቱ ፖለቲካ ተመቾም አልተመቾ፥ ለአቋማቸው መሠረት ያደረጓቸው መርሆች ትክክለኝነት አጥፌ ሊያሰኛቸው የሚችል ካለመሆኑ አልፎ፥ ውሎ አድሮ፥ አቋሞቻቸው የመንግሥትም እንዲሆኑ አስደርጓል።

ለምሳሌ፥ ከላይ የተጠቀሰውን የውሳኔ ሐሳብ ደጋፊ አግኝተው ማንቀሳቀስ እንደጀመሩ፥ ምዕራባውያኑ ሀገሮች አዲስ አበባ በመደቧቸው አምባሳደሮቻቸው አማካይነት በቀጥታ ጉዳዩን ለንጉሠ ነገሥቱ አቅርበው ነበር። ሐዲስም የውሳኔ ሐሳቡን እንዲያነሡ በመንግሥታቸው ተጠይቀዋል። እንዲያውም መመሪያም አልጠየከበትም ተብለው ነበር። ነገር ግን፥ 'በመርዝ ወይም በመስታርድ ጋዝ፥ የተጠቃችው ብቸኛዋ ኢትዮጵያ ከማንኛቸውም አገር ይበልጥ፥ የእንደዚህ ዐይነት የሰው ዘር በገፍ የሚፈጁ መሣሪያዎችን መሠራት ማውገዝ ዐይነተኛ አቋሟ ነው በማለት ላቀረብኩት'፥ የተለየ መመሪያ መጠየቅ ያለብኝ አልመሰለኝምና ነው፥ የሚል መልስ ነበር ያቀረቡት። ኋላ መንግሥትም ይኸን

አቋም ይዞ ነው የውሳኔ ሐሳቡ በተመድ ለድምጽ ሊቀርብና ተቀባይነት ሊያገኝ የበቃው።

ሐዲስ በዚህ ጉዳይ ያሰቡት የቃል ኪዳን ስምምነት ባይፈረምም፥ እንዳችም መሣሪያ አምራች ያልሆነችው ኢትዮጵያ የተባበሩት መንግሥታት የጦር ቅነሳ ጉባዔ አባል አገር እንድትሆን ያስመረጣት ምክንያት ቢያንስ አንዱና ዋናው ሳይሆን አይቀርም ብሎ ለመገመት የሚያስችል ይመስለናል።

ሰኔ 3 ቀን፥ 1952፥ "ሐዲስ ዓለማየሁ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴታ"[41] ተብለው አዲስ አበባ ይመለሳሉ፥ ከሦስት ዓመት ያነሰ ጊዜም ቢሆን፥ በተባበሩት መንግሥታት ዘለቄታ ያላቸውን ተግባራት ከውነዋል።

ይህ በሆነ ከስድስት ወር በኋላ የታህሣሡ የነመንግሥቱ ንዋይ የመንግሥት አመራርና አሠራር ለውጥ ሙከራ ይካሔዳል። ሙከራው ብዙ ጊዜ ሳይቆይ ወዲያው በማክተሙ፥ በብዙዎች ዘንድ ወዲያው የተረሣ ነበር። እንዲያውም፥ የንጉሠ ነገሥቱ ሥልጣን የማይነቃነቅ ተራራ መሆኑን አዲስ ማረጋገጫ አድርገው የወሰዱት የሚበዙት ናቸው። እጅግ በጣም ጥቂቶች፥ ለምሳሌ፥ እንደ ሌፍትናንት ጄኔራል ዐቢይ አበበ (*አውቀን እንታረም*) 'እርማት እንኳ' ማድረግ ማስፈለጉን ተገንዘቡ። ወይም ይህን ስሜታቸውን በቻሉት መንገድ ለመግለጽ የሞከሩ። ". . . እዚህ ጽሑፍ ውስጥ የሰፈሩት አነጋገሮች ሊነቀፉም፥ ሊያስነቅፉም፥ ሊያከራክሩም ይችሉ ይሆናል፤ ነገር ግን . . . በንጹሕ ሕሊና ብቻ በመመራት፥ ወደፊት የሚጠብቀንን በመገመት . . . ተባብረን ለውድ ሀገራችን የእውነት አገልግሎት ማበርከት እንዳለብን ማሳሰቤ ነውና፥ 'አውቀን እንታረም'።"[42] ሌሎቹ ግን 'ያለፈው ዐለፈ' ያሉ ይመስሉ ነበር።

ሁኔታውን እንደ አደጋ ምልክት ቆጥሮ መሠረታዊ ለውጥ በአጣዳፊ ማድረግ የሚጠይቅ የነበረ መሆኑን መገንዘብ ብቻ ሳይሆን፥ በጽሑፍ ለንጉሠ ነገሥቱ ለራሳቸው መግለጽ አስፈላጊ መሆኑን እንደ ሐዲስ ዓለማየሁ ግን የተረዳ ያለ አይመስልም።

ጥር 23 ቀን፥ 1953 ይኸንኑ አስመልክቶ ማስታወሻ ጽፈው ለንጉሠ ነገሥቱ አቀረቡ። ከዚያ ውስጥ አንዳንድ ነገሮች እንጠቅሳለን፤

> ማናቸውም ነገር መነሻ ምክንያት ሳይኖረው እንዲሁ ከደልዳላ ሜዳ አይፈልቅም . . . ምክንያት የሆኑትን ነገሮች በጊዜ መርምሮ ካላስወገዷቸው ይዋል ይደር እንጂ ሁከት መነሣቱ አይቀርም. . . .[43]

በማለት ነገሩ በቀላሉ ማለፉን ብቻ አይቶ፥ ምንም ነገር እንዳልሆነ ቆጥሮ ወደ ቀድሞው ሁናቴ በመመለስ መቀጠል አደገኛ ነገር እንደሚያስከትል ከጠቆሙ በኋላ፥ አጽንኦት በመስጠት፥

> . . . ሥሩ እንደተደበቀ ተቀምጦ፥ ከላይ የሚታየውን ቅርንጫፉን ብቻ ቢጨፈጭፉትና፥ ለጊዜው እንኳ የጠፋ ቢመስል፥ የተመቸ ጊዜ ሲያገኝ . . . ዳብሮ፥ ተስፋፍቶ፥ ለማጥፋትም እንደሚያስቸግር ሆኖ በብዛትና በብርታት ይነሣል::[44]

ከዚያ፥ ንጉሠ ነገሥቱ እስከዚያ ድረስ የፈጸሟቸውን ዐበይት ተግባራት ሙሉ ዋጋ ሰጥተው፥ ዘመኑ የሚጠይቀውንና ኢትዮጵያ በዚያን ጊዜ የደረሰችበትን፥ በተለይም በፖለቲካው መስክ የሚታዩትን ቀርነቶች ጠቁመው፥ የለውጥ አቅጣጫዎች ያመለክታሉ::

ይህን፥ የነበረውን ሥርዓት ጉድለቶችና የለውጥ አማራጭ የሚያቀርብ ዐሥራ ሦስት ገጽ ጽሑፍ እንደሚገባው በዚች ጽሑፍ ተንትኖ ለማቅረብ ስለማይመች፥ አንድ ሁለት ነጥቦች ብቻ ጠቅሰን ለጊዜው እናልፈዋለን::

የችግሩ ሁሉ መነሻ ሕገ መንግሥቱ እንደሆነ፥ በጥቂት፥ ግን መሠረታዊ ቁም ነገር በሚያመለክቱ ምሳሌዎች 'ማስታወሻው' ሲያቀርብ፥ ከነዚህ አንዱ የሚከተለው ነው፤

> ዛሬ፥ ከዓለም ውስጥ በሬፐብሊክ መንግሥት የሚተዳደሩት አገሮች ቀርተው፥ በንጉሠ ነገሥት፥ በንጉሥና በፕሪንስ ከሚተዳደሩት አሥራ ሰባት አገሮች መሐከል እንኳ፥ በጣም የሚበዙት አገሮች ሕገ መንግሥቶች፥ የመጨረሻው የመንግሥት ሥልጣን የሚመነጨው ከሕዝብ መሆኑን ሲያውጁ፥ የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት (አንቀጽ 26) የሥልጣን ምንጭ ንጉሠ ነገሥቱ መሆናቸውን ስለሚያውጅ፥ ይህ፥ ኢትዮጵያ የፖለቲካ መብት በሙሉ ለሕዝብ ባልተሰጠበት፥ በመሐከለኛው ዘመን የምትኖር ለመሆንዋ አንድ ምልክት ነው . . . ."[45]

ስላቀረቧቸው ሐሳቦች ደግሞ እንዲህ ይላሉ፤

> በዚህ ማስታወሻ ያቀረብሁትና፥ እሱን የመሳሰለ የማሻሻል አሳብ ሁሉ . . . በሌሎች አገሮች ሲሰበክ ያልኖረ ወይም ያልተደረገ አዲስ ነገር አይደለም። በኢትዮጵያም ዛሬ ባይሆን ነገ፥ በግርማዊነትዎ ጊዜ ባይሆን በሌሎች መደረጉ አይቀርም. . . .(46)

ሲደመድሙም፥

> በዚህ ማስታወሻ የገለጽኳቸው አንዳንድ ነገሮችና የገለጽሁበት ቋንቋ ትንሽ መረር ያሉ መሆናቸው ይሰማኛል። እንዲሁም፥ ሰው ሆኖ ለተፈጠረ ሁሉ፥ ከመራራ እውነት የተቀመመና የለዘበ ከንቱ ውዳሴ እንደሚጣፍጥ ዐውቃለሁ። ነገር ግን፥ ዞሮ ዞሮ ከንቱ ውዳሴ የሚያፈራውን ጣፋጭ ፍሬ የሚለቅሙና በሱም የሚጠቀሙ አሞጋሾቹ ብቻ በመሆናቸው፥ ተሞጋሾቹ ሁልጊዜም ቢሆን ከመራራው እውነት ጋር ቀሪዎች ናቸው . . . .[47]

ማስታወሻውን በሚመለከት፥ አቅራቢው ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ቃላት ተለዋውጠውባቸው፥ ፀወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ስብሳቢነት በኮሚቴ ታይቶ የማሻሻያ ሐሳቦቹ እንዴት እንደሚሆኑ ይመከርበታል የሚል መልስ ቢሰጥም፥ ስብሳቢው ኮሚቴውን ሳይሰበስቡ ይቀራሉ።

ሆኖም በ1958፥ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የራሱን የካቢኔ አባላት ይመርጥና ያሾማል የሚለው ዐዋጅ መውጣት፥ ከዚህ ማስታወሻ የለውጥ ሐሳቦች እጅግ የራቀ ቢሆንም፥ የዚያ ግፊት የርቀት ተጽእኖ አልነበረው ይሆን? የሚል ሐሳብ ያጭራል። ስለ የማሻሻል ለውጡ፥ በፈራ ተባ ሲዘገም፥ የተፈራው ይደርሳል - 1966!

የካቲት 2 ቀን፥ 1953፥ ክቡር ዶክተር ሐዲስ ዓለማየሁ፥ በያዙት ደረጃ፥ "በትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር፥ ሚኒስትር ዴታ" ሆነው ይሾማሉ።[48] በአዲሱ ቦታ በሚኒስትር ፈንታ የቅርብ አለቃቸው ቀጥታ ንጉሠ ነገሥቱ ይሆናሉ። ይኸ ሁኔታ ብዙ የማያስኬድ መሆኑ ግልጽ ነበር። ንጉሠ ነገሥቱ፥ ስለ ትምህርት እንደ ሚኒስትር የራሳቸው ሐሳብና አካሔድ የነበራቸው ሲሆን፥ ሐዲስም ስለ ትምህርቱ ሥርዓት አወቃቀርና ይዘት ጭምር የራሳቸው ጽኑ እና ከነበረው ጋር በቀላሉ የማይጣጣም እምነት የነበራቸው ለመሆኑ ከላይ ያለን ጥቆማ በቂ ይመስለናል። ከበጀት ማነስ ያላነሰ፥ የሚፈቀደው በጀት አደላደል (በዋና መሥሪያ ቤቱና ዐይነተኛ ሥራውን በሚሠሩት ዘርፎች መካከል) የተዛባ የነበረ መሆኑም ክቡር ዶክተር ሐዲስ የሚቀበሉት አልነበረም። በመሆኑም፥ ሥራውን ለመተው ወስነው ስንብት ይጠይቃሉ።

ሆኖም፥ ሐምሌ 26 ቀን፥ 1953፥ "በሎንዶን የግርማዊነታቸው ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደርና ልዩ መልእክተኛ"[49] ተብለው እንደገና በውጭ ሀገር ለሥራ ይመደባሉ። እስከ 1958 እንግሊዝ አገር በለንደን ይቆያሉ። ተቀማጭነታቸው ለንደን ይሁን እንጂ፥ ከእንግሊዝ አገር በተደራቢ፥ በኔዘርላንድ የኢትዮጵያ አምባሳደርም ሆነው ተሾመው ነበር።

ከመደበኛ የሥራ ኃላፊነታቸው ውጭ፥ በድርሰት ረገድ ሁለት ሥራዎች ላይ አተኩረው ነበር። አንዱ፥ ዘለግ ላለ ጊዜ ትተውት ወደ ነበረው የተውኔት ድርሰት በመመለስ፥ *'ወንጀለኛው' ዳኛን* መጻፍ መጀመር ሲሆን፥ ሁለተኛው ሐምሌ 19 ቀን፥ 1955 የተጠናቀቀው፥ *ኢትዮጵያ ምን ዐይነት አስተዳደር ያስፈልጋታል?* የሚለው፥ ቀደም ሲል ለንጉሠ ነገሥቱ ባቀረቡት ማስታወሻ ውስጥ በቀረበው የለውጥ ሐሳብ ላይ የተመሠረተው ጽሑፍ ነበር።

*'ወንጀለኛው' ዳኛ*፥ እንደሚታወቀው፥ በ1974 ሲታተም፥ ወደ ረዥም ልቦለድነት ተቀይሮ ይሁን እንጂ፥ ተጸንሶ የተወለደው በተውኔት መልክ ነበር። *ኢትዮጵያ ምን ዐይነት አስተዳደር ያስፈልጋታል?* የሚለው፥ በየካቲት ወር 'በግብታዊነት' ለፈነዳው የለውጥ ማዕበል አግጣጫ አመልካችና መወያያ እንዲሆን ታስቦ፥ በ1966 በግንቦት ወር ታትሞ ወጣ። ሲታተም፥ በመጽሐፉ ውስጥ የሰጡትን "*መግለጫ*" ሲደመድሙ እንዲህ ይላሉ፤

> አንባቢዎች እንደምትመለከቱት፥ በዚች መጽሔት የቀረበው አሳብ ከተጻፈ አሥራ አንድ ዓመት ሊሆነው ምንም ያህል አልቀረው። ነገር ግን፥ ዛሬ ለገጠመን ችግር በሙሉ ባይሆን <u>በከፊል የሚያገለግል አሳብ ይኖርበት እንደሆነ ለንግግር ማቅረቡ አይከፋም</u> በማለት አሁን ያሳተምሁት በዚህ ምክንያት ነው።[50]

ሆኖም፥ ያ ወቅት ሥር ነቀል ለውጥ ያስፈልጋል ተብሎ ሕዝብ የተቀሰቀሰበት ሁኔታ ስለነበር፥ ተወያይቶ ለመጣልም ሆነ ለመቀበል ጊዜው የሚፈቅድ አልነበረም። እንዲያውም፥ ቀንና ዓመተ ምሕረት ባልተመለከተበት፥ ከወቅቱ ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር እንኳ ሲታይ ራሱም "ግራ-ቀደም" ሊሰኝ በሚችል፥ በንግድ ማተሚያ ቤት በታተመ ጽሑፍ፥ ደራሲው፥ የሐዲስን አቀራረብ ባልተረዳ ወይም ለመረዳት ባልፈቀደ መንፈስ ዘለፋ እንዲያዥጎደጉድ ጋበዘ።[51]

ይሁንና፥ በ1958 በወጣው ዐዋጅ መሠረት፥ ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ መጋቢት 15 ቀን፥ 1958 ጠቅላይ ሚኒስትርና የጽሕፈት ሚኒስትር ሆነው ተሾሙ። "አዲስ" ተብሎ ባቋቋሙት ካቢኔ ውስጥ ክቡር ዶክተር ሐዲስ ዓለማየሁ፥ ከለንደን ወደ አዲስ አበባ ቀደም ሲል መጥተው ነበርና፥ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሲጠይቋቸው ተስማምተው፥ "የፕላንና ልማት ሚኒስትር" ሆነው ግንቦት 3 ቀን፥ 1958 ተሾመው ነበር።[52]

በአዲሱ ዐዋጅ መሠረት፥ የገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣንና ኃላፊነት ከአዲሱ የፕላንና ልማት ሚኒስቴር ሥልጣንና ኃላፊነት ጋር የሚያነካኩ አንቀጾች ነበሩበት። አንቀጾቹ ባጠቃላይ በበጀት ጉዳይ፥ በተለይ የልማቱን በጀት

ዝግጅትና ማስፈቀድን፥ እንዲሁም የውጭ ብድርና እርዳታን በሚመለከት ሁለቱን መሥሪያ ቤቶች የሚያሟግቱ ነበሩ።

የሆነው ሆኖ፥ ሦስተኛው የአምስት ዓመት (በገንዘብ ሚኒስቴር ዐይን ካቅም በላይ ነው ሲባል የነበረው) ፕላን ተዘጋጀ። ሆኖም፥ በአፈጻጸም ችግር በመፈጠሩ እና ለልማት የሚፈቀደው ያገር ውስጥ ገንዘብ በጀት በፕላኑ ከተመለከተው እያነሰ በመሔዱ፥ ሐዲስ ፍጹም ስንብት ቢጠይቁ፥ ጥር 11 ቀን፥ 1961 'የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባል' እንዲሆኑ በመደረጉ፥[53] ከመንግሥት አስፈጻሚው ዘርፍ ለዘለቄታው ወጡ። ከምክር ቤቱም፥ በ1966 ስድሳ አራተኛ ዓመታቸውን ካከበሩ ከተወሰኑ ሳምንታት በኋላ ጡረታ ጠይቀው ወጡ።

በጥር ወር ተጭሮ በየካቲት ወር የፈነዳው ሕዝባዊና 'ግብታዊ ዐመፅ'፥ በሰኔ ወር ወታደራዊ ቡድን እንዲነሣ ሁኔታዎችን ፈጠረ። 'ደርግ' በመባል የሚታወቀው፥ በጠቅላላ 151 አባላት የነበሩት ወታደራዊ ኮሚቴ፥ የእንቅስቃሴውን ጉዞ መቆጣጠር ጀመረ።[54] ልጅ እንዳልካቸው መኮንንን ከሥልጣን ካወረደ በኋላ፥ ክቡር ዶክተር ሐዲስ ዓለማየሁን በሳቸው ቦታ ለማድረግ አስቦ ሲጠይቃቸው፥ በደስታ ፈጥነው የሚቀበሉ ሳይመስለው የቀረ አይመስልም። ምክንያቱም፥ ከመቀበላቸው በፊት፥ የጠቅላይ ሚኒስትሩ የሥልጣንና የኃላፊነት መጠንና ገደብ ምንድርነው?፥ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሥራ ላይ የሚያውለው ፕሮግራም ምንድርነው? የሚል መንፈስ ያላቸው ጥያቄዎች ሲያቀርቡ፥ የደርጉ ሊቀ መንበር አጥጋቢ መልስ አልነበራቸውም። ስለዚህ ሐዲስ ሹመቱን አልቀበልም አሉ።

ነገር ግን፥ ሰኞ ሐምሌ 15 ቀን፥ 1966፥ የደርጉ ተወካይ ለንጉሠ ነገሥቱ ጉዳዩን እንደሚከተለው እንዳቀረበው፥ በማግሥቱ የወጣው *አዲስ ዘመን* ጋዜጣ ዘግቦታል፤

> ግርማዊ ሆይ! ኢትዮጵያና ሕዝቦቿ በከፍተኛ ችግር ላይ ባሉበት የፈተና ጊዜ፥ የአስተዳደሩ ሥልጣን ከሲቪሉ እጅ እንዳይወጣ በማለት ክቡር አቶ ሐዲስ ዓለማየሁ የጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ሥልጣን እንዲረከቡ ጠይቀናቸው ኃላፊነቱን ለመሸከም ፈቃደኛ አልሆኑም[54]

በማለት፥ ትክክለኛውን ሥዕል በማያንፀባርቅ አኳኋን ገልጾት ይገኛል። ከዚያ በኋላ፥ ልጅ ሚካኤል እምሩ የጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ኃላፊነት ከያዙ በኋላ፥ ምንም ያህል ጊዜ ሳይቆይ፥ ከ"ሲቪሉ እጅ እንዳይወጣ" ብለን የተባለው "ተዘንግቶ" መስከረም 2 ቀን፥ 1967 ደርግ ሥልጣኑን አጠቃልሎ ያዘ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩንም መጀመሪያ የማስታወቂያ ሚኒስትር፥ ኋላም የፖለቲካ አማካሪ አድርጎ መደበ።

ደርግ 48 አባላት የሚኖሩበት የመማክርት ሸንጎ ሲያቋቁም፥ ከመማክርቱ መካከል ክፍለ ሀገሮች የሚመርጧቸው የተወሰኑ ነበሩ። ከነዚህ መካከል ጎጃምን እንዲወክሉ በጎጃም ሕዝብ ክቡር ዶክተር ሐዲስ ዓለማየሁ መመረጣቸውን ጥቅምት 9 ቀን፥ 1967 የወጣው *አዲስ ዘመን* ጋዜጣ ያመለክታል። የመማክርት ሸንጎው እስኪበተን ድረስ ከአንድ ዓመት ተኩል በላይ፥ ይመጣል የተባለውን ተኪያቸውን ሲጠብቁ በሸንጎው ቆዩ።

በዚህ በድህረ 1966 ወቅት፥ የዶክተር ሐዲስ ዓለማየሁ ዋናው ያስተዋጽኦ አግጣጫ በአማርኛ ጥበበ ቃላት በኩል ነበር። በ1958 ለመጀመሪያ ጊዜ ታትሞ የነበረው ታላቁ የልቦለድ ሥራቸው፥ *ፍቅር እስከ መቃብር* ደጋግሞ (7 ጊዜ) ከመታተሙም በላይ፥ '*ወንጀለኛው ዳኛ*' 3 ጊዜ፥ *የልምዣት* 2 ጊዜ ታትመው፥ በአንባቢው ሕዝብ ዘንድ በብዛት ተሠራጩ። ከሕይወት ታሪካቸው ውስጥ የፋሺስት ወረራን ወቅት የሚመለከተውን ብቻ ቀንጭቦ የያዘው መጽሐፍ፥ *ትዝታ*፥ በ1985 ታትሞ ወጣ። በአጠቃላይ፥ የብዕር በረከታቸው በሕዝብ ዘንድ በዚህ ወቅት ጎልቶ ታየ። ከዚያ ቀደምም ቢሆን በምሁራን ዘንድ፥ በ*ፍቅር እስከ መቃብር* ብቻ እንኳ፥ የደራሲነት ልካቸው ታውቆና ታምኖበት እንደ ነበር የሚታወቅ ነው።

በ*ፍቅር እስከ መቃብር* "የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ሽልማት" በሥነ ጽሑፍ ተሸልመውበታል። ያን ጊዜ ሽልማቱን ከተቀበሉ በኋላ፥ እንደ ደንቡ መሠረት ንግግር አድርገው ነበር። የንግግሩ ይዘት፥ በዓለም ላይ የበላይነትን ለመያዝ "በብዕርና በሰይፍ" መካከል ሲካሔድ ስለኖረውና ስለሚኖረው ትግልና የኋላ የኋላ የብዕርን ኃያልነት የሚያመለክት ነበር።

ይኽን ፍሬያማ የብዕር አዝመራቸውንና ያስገኘውን መልካም ውጤት ዕውቅና በመስጠት፥ ቀደም ሲል ሴኔቱ በወሰነው መሠረት፥ ነሐሴ 27 ቀን፥ 1991፥ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የክብር ዶክተርነት ዲግሪ፥ በከፍተኛ የዩኒቨርሲቲው ተወካይ በመኖሪያ ቤታቸው ተሰጣቸው።

ዛሬ (መጋቢት 1993)፥ ክቡር ዶክተር ሐዲስ ዓለማየሁ ዘጠና አንደኛ ዓመታቸውን ጥቅምት 7 ቀን 1993 አክብረው፥ ጤናቸው በፈቀደ መጠን፥ ከዕውቀታቸውና ከልምዳቸው ቁም ነገር ፈላጊዎች ለሆኑ ሁሉ በማካፈል ላይ ይገኛሉ።

## ማስታወሻዎች

[1] ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ፥ *የሕይወት ታሪክ (Biographie) በኋላ ዘመን ለሚነሡ ልጆች ማስታወቂያ፡* አ. አ. ልዑል ተፈሪ ማተሚያ ቤት፥ 1915።

[2] *መንግሥቱ ለማ፥ ደማሙ ብዕረኛ (ግለ-ታሪክ)* በመስፍን ዓለማየሁ አርታኢነት፥ በሜጋ አሳታሚ ድርጅት አሳታሚነት በ1988 በወጣ መጽሐፍ ክፍል አንድ ውስጥ ከሚገኘው ጽሑፍ፥ ገጽ 18።

[3] *የየልምዣት ኅትመትና፥ የተረት ተረት የመሠረት* ሁለተኛ ክፍል ድርሰት ከተጠናቀቀ በኋላ በነበረው ወቅት፥ በኩራዝ አሳታሚ ድርጅት ምክትል *ሥራ* አስኪያጅ፥ የሕይወት *ታሪካቸውን* የመጻፍ ጉዳይ እንደ ገና ይነሣል። በዚህን ወቅት ነበር፥ ሌላው ቀርቶ፥ በወጋቸው መካከል በየጊዜው እንዲጋጣሚ ስለሚነሣው የማይጨው ጦርነት፥ የአርበኝነት ጅማሮና በኢጣሊያ የግዞት ዓመታት ጉዳይ ላይ እንዲጽፉ ለማሳመን የተቻለው። አንዴ የመወሰኑ ጉዳይ ነበር እንጂ ከተወሰነ በኋላ ግን ከባዱን *ሥራ* በትጋት ተያይዘውት በአንጻራዊ ደረጃ ባጭር ጊዜ አጠናቀቁት - *ትዝታን*።

[4] *ከየልምዣት የመጀመሪያ* እትም ቀደም ብሎ ለአስፋው ዳምጤ በጭውውት መካከል ትክክለኛው የልደት ዘመናቸው 1902 *መሆኑንና*፥ እስከዚያን ጊዜ (1980 አካባቢ) በይፋ የሚገለጸው 1906 ስህተት *መሆኑን* ከዓመታት በፊት እንዳረጋገጡ ነግረውት ነበር። ሆኖም፥ በግል የተነገረው መስሎት ያንኑ በይፋ *ታውቆ* የኖረውን (1906) በመጽሐፉ ላይ እንዲወጣ አድርጎ ነበር። ደራሲው ያን አይተው፥ ትክክለኛው በሁለተኛው እትም ላይ እንዲወጣ አደረጉ።

[5] *ፍካሬ (መጽሔት)*፥ አንደኛ ዓመት፥ ቅ.1፥ ቁ.1፥ የካቲት 1985፥ ገጽ 4።

[6] ዝኒ ከማሁ።

[7] ዝኒ ከማሁ።

[8] አለቃ ይሄይስን ከብዙ ጊዜ በኋላ፥ ክቡር ዶክተር ሐዲስ ዓለማየሁ፥ ባንድ ወቅት የጎጃም እንደራሴ እነበሩት፥ ልዑል ራስ እምሩ ቤት እዚህ ያገኟቸዋል። በጭውውት መሐል ሐዲስ ይኸን ነገር ቢያነሱባቸው፥ 'እንዴት ይኸን አደርጋለሁ፤ አላደርግም' በማለት እንዳላመኑላቸው ይናገራሉ። ዘመኑ በመርዘሙ ተረስቷቸው ይሁን ወይም በሌላ ምክንያት፥ ነገሩን 'አለማመናቸው' ሐዲስን ትዝ ባላቸው ቁጥር ያስገርማቸዋል። (አለቃ ይሄይስ በቅባትነታቸው የታወቁና ጸንተውበት የኖሩና "አሁን በኛ ዘመን" ያረፉ መሆናቸውን ከአንድም ሁለት ሰዎች ለዚች ጽሑፍ አቅራቢ ነግረውታል።)

[9] አማኑኤል አብርሃም፥ *የሕይወቴ ትዝታ*፥ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፥ አ.አ. 1992፥ ገጽ፥ 6-7።

[10] ከላይ የተጠቀሰው፥ ገጽ 7።

[11] ከላይ የተጠቀሰው፥ ገጽ 8።

[12] ቄስ ባድማ፥ *ብርሃንና ሰላም*፥ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር 42፥ ጥቅምት 6 ቀን፥ 1923። ቄስ ባድማ ይህን አስታውሰው የጻፉት፥ ከሦስት ዓመት በኋላ እነዚያ የሐዲስ ጓደኞች፥ ". . . ሦስት ዓመት ያህል በተፈሪ መኮንን ተማሪ ቤት ሲማሩ ቆይተው፥ ከፍ ያለ ትምህርት እንዲያገኙ፥ በመስከረም 28 ቀን፥ 1923 ወደ ቤይሩት [ራስ ኃይሉ] ሰደዷቸው" የሚለውን ዜና ሲያበስሩ ወደ ኋላ ተመልሰው ስለ ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት አገባባቸው ለማስታወስ ሲሉ ነበር።

[13] ብላታ መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ፥ *የአማርኛ ሰዋስው*፥ 1935፥ "መቅድም"፥ ገጽ 3።

[14] ብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል፥ *ዝክረ ነገር*፥ 1942፥ ገጽ 599።

[15] ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ፥ *ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ፥ አንደኛ መጽሐፍ*፥ 1965፥ ገጽ 49።

[16] ለተፈሪ መኮንንና ዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤቶች የተሰጡት ደንቦች የመጨረሻ ቅርፃቸው በ*ዝክረ ነገር* ውስጥ ተመዝግቦ ይገኛል። (ከገጽ 599-626 ይመልከቱ።)

[17] በዚያን ጊዜ የዛሬው የትምህርት ሚኒስቴር፥ "የትምህርትና የጥበብ ሚኒስቴር" ይባል የነበረ ሲሆን፥ የወጣቱን ቲያትር ይሁንታ የነሡት ባለሥልጣን "ሚኒስትር" አልነበሩም። በወቅቱ 'ሚኒስትር' ሳይኖር፥ በዋና ዲሬክተርነት፥ አቶ ሣህሌ ፀዳሉ የበላይ ሆነው የሚመሩት ሚኒስቴር ነበር። አቶ ሣህሌ ፀዳሉ፥ "ብላቴን ጌታ" የሚለውን ማዕረግ ያገኙት፥ በ1923 ጥቅምት 23 ቀን፥ በአዲሱ ሕገ መንግሥት ለታወጀው የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት "ሁለተኛ አለቃ" ሆነው በ1924 ሲሾሙ እንደ ነበረ፥ *ብርሃንና ሰላም* (7ኛ ዓመት፥ ቁ.45) በጥቅምት 25 ቀን፥ 1924 እትሙ ሲገልጽ፥ በጥር 4 ቀን፥ 1925 እትሙ ደግሞ፥ ከሕግ መወሰኛ ምክር ቤት ምክትልነት "ብላቴን ጌታ ሣህሌ ፀዳሉ የትምህርትንና የጥበብን ሚኒስትርነት ተሾሙ" ይላል።

[18] አማኑኤል አብርሃምም፥ በ*የሕይወቴ ትዝታ*፥ 1992፥ ገጽ 9 ላይ፥ አቶ ሣህሌ ፀዳሉን (ያኔ ዋና ዲሬክተር የነበሩትን) "ሚኒስትሩ" ብለው እንደሚጠቅሷቸው፥ አቶ ሐዲስም በ*ትዝታ* ውስጥና በንግግራቸው ደጋግመው ይጠቅሱታል።

[19] ሐዲስ ዓለማየሁ፥ *ትዝታ*፥ 1985፥ ገጽ 141።

[20] ሐዲስ ዓለማየሁ፥ *ትዝታ*፥ 1985 ምዕራፍ 18፥ ገጽ 140-44። ቢትወደድ ወልደ ጻድቅ፥ እዚህ ላይ እንደተገለጸው በኅሬ የተመሠረተው የኢትዮጵያ መንግሥት "ጠባቂ" ሳሉ የሆነ ሲሆን ቲያትሩ በታየበት ወቅት ግን ደጃዝማች በሚል ማዕርግ የአገር ግዛት ሚኒስትር ነበሩ። በዚህ መካከል፥ በ1923 በታወጀው ሕገ መንግሥት መሠረት ለተቋቋመው ምክር ቤት የሕግ መወሰኛው የመጀመሪያ "ዋና አለቃ (ሰብሳቢ) ሲሆኑ፥ በጥቅምት ወር 1924 "ቢትወደድ" ተባሉ። (*ብርሃንና ሰላም* 25/2/24።)

[21] *ብርሃንና ሰላም*፥ 7ኛ ዓመት ቁጥር 38፥ ሐሙስ መስከረም 6 ቀን፥ 1924 ዓ.ም.፣ *ብርሃንና ሰላም* 8ኛ ዓመት ቁጥር 4፥ ሐሙስ ጥር 12 ቀን፥ 1924 ዓ.ም.፣ እንዲሁም፥ *ትዝታን* (በማስታወሻ ቁጥር 20 በተጠቀሱት ገጾች ላይ) ይመለከቷል።

[22] አሌክሳንድሮ ዲ. ባዮ፥ *ቀይ አንበሳ* 1929 (1937 እ.ኤ.አ.)፥ ትርጉም ዶክተር ተስፋዬ መኮንን (1992)፥ ገጽ 31፣ "ሆቴሉ ደረስን። ባለሁለት ፎቅ ቤት ነው። 'ማጀስቲክ' ይባላል። ባለቤቱም አንድ ግሪካዊ ነበር . . . "እኔ ፓፓታኪስ እባላለሁ። የዚህ የማጀስቲክ ሆቴል ባለቤት ነኝ'. . ." ብሎ እንደነገረው ይገልጽልናል ጸሐፊው። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ከ12 ገጾች በኋላ፥ በአራዳ ጊዮርጊስ አካባቢ ዛፍ ላይ ስለሚሰቀሉ ወንጀለኞች ሲጽፍ፥ ከሆቴሉ አካባቢ እንደማይርቅና፥ ጸሐፊው ሲያልፍ ሲያገድም እንደሚያየው አድርጎ ነው የሚተርከው።

[23] *ትዝታ*፥ ገጽ 144።

[24] *ብርሃንና ሰላም*፥ 8ኛ ዓመት፥ ቁ.22፥ ሐሙስ ግንቦት 18 ቀን 1924 ዓ.ም። እዚህ ላይ ሁለት ቁምነገሮች ማከል ይገባል። የመጀመሪያው፥ የጋዜጣው ዘገባ ቲአትሩን ያቀረቡት "የተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ተማሪዎች" ናቸው ነው የሚለው። ቀደም

ሲል በ*ትዝታ* ውስጥ ከ"የሐበሻና የወደኋላ ጋብቻ" መታየት አስቀድሞ፥ ሐዲስ በአድማ ጠንሳሽነት ጥርጣሬ ከ18 ዓመት በላይ ዕድሜ ካላቸው ጋር በተመላላሽ ተማሪነት በመመደባቸው፥ የ1924ቱን የመጨረሻ (የ6ኛ) ክፍል ትምህርታቸውን ለማቋረጥ በ1923 ክረምት መወሰናቸውን (ዝርዝሩን ባይገልጹም) ተገንዝበናል። ታዲያ፥ በግንቦት 1924 የተፈሪ መኮንን ተማሪዎች ቲያትር ሲያቀርቡ፥ ከአዘጋጆቹ አንዱ እንዴት ሐዲስ ሆኑ ያሰኛል። "የሐበሻና የወደኋላ ጋብቻ" ሁለቴም ሲታይ በተፈሪ መኮንን ተማሪዎች እንደቀረበ ተደርጎ ነበር በጋዜጣ የወጣው። እንዲያውም፥ *የብርሃንና ሰላም* (ጥር 12 ቀን፥ 1924) ዘገባ፥ ቲያትሩ ከሦስት፥ አጠር ካሉ ቲያትሮች በኋላ፥ 4ኛ ሆኖና ርእሱም፥ "ያቶ ወደኋላ ሞት በኃይለ ሥላሴ" ተብሎ በተማሪዎቹ እንደቀረበ ነበር ያተተው። ለዚህ እንቆቅልሽ መሳይ ጉዳይ፥ ከሐዲስ ጓደኞች መካከል፥ የከተማ ልጆች የሆኑት ትምህርታቸውን ቀጥለው የነበረ መሆኑና፥ በቲያትር ከትምህርት ቤት ውጪም ይሳተፉ የነበረ መሆኑ ነው መፍቻው። ሁለተኛው ቁም ነገር፥ ለሠርጉ ስለቀረቡት ቲያትሮች ጋዜጣው፥ "... የትያትሩን ነገር ለመጻፍ ብዙ ስፍራ የሚይዝ ስለ ሆነ" በማለት ያልፍና፥ "ከአቶ ዮፍታሔ ንጉሤ የተገጠሙትን ድንቅ አማርኛ ያለባቸውን ግጥሞች በሚከተለው መስመር ጽፈናቸዋል" ብሎ ማቅረቡ ነው። ታትመው የሚገኙ የዮፍታሔ ሥራዎች ብርቅ ስለሆኑ፥ እነዚህን አምስት 'መንቶች' እና ስድስተኛውንም ባለአራት ቤት ግጥም ከዚህ ቀጥለን ማስፈር ወደድን፤

1. ፍሬውንም አየን በዘለላው አምሮ።
   እጅግ መልካም ነበር አበባው ተድሮ።
2. የሰው ወርቅ አያደምቅ ይላል ሰው ተላላ።
   የእኛ ወርቅ ምነው ታደምቃለች ሌላ።
3. ኀፍረት የሌለው ሰው እንደዚህ ልጅ የታል።
   ምን አባቱን ሁኖ ሰው ይመለከታል።
4. ምን አስፈራው ያን ልጅ በጥቂት ሰው ፊት።
   በብዙ ሰው መሃል ገናና ሲሉት።
5. መቋሚያ ነው ስንል ሲቀበል ከአባቱ።
   ከዘራ አይደለም ወይ የያዘው በጣቱ።
6. ውቢቱ ሙሽራ ከሰፋችልን።
   መሶብና አገልግል እናቀርባለን።
   ሙሽራችን ምረጥ የምትገዛውን።
   ሁለቱን አገልግል ትገዛ እንደሆን።

[25] ይልማ ዴሬሣ (አርታኢ)፥ *ያዲስ ዘመን መዝሙር*፥ 1933፥ "መቅድም"። በመቅድሙ ውስጥ የቀረበው የልዩ ልዩ ዐይነት ድርሰት "አቅርቡልን" ጥሪ፥ ቀደም ብሎ በጋዜጣ በርእስ ጉዳይ ተከፋፍሎ ተከታትሎ የወጣ ነበር።

[26] *ትዝታ*፥ ገጽ 18።

[27] (ገብረ) ሕይወት ሕዳሩ፥ *ያቺም ቀን ተረሳች* (1925-33)፥ ገጽ 5።

[28] *ትዝታ*፥ ገጽ 19።

[29] *ትዝታ*፥ ገጽ 28-29።

[30] *ትዝታ*፥ ገጽ 150።

[31] ፈለቀች እሸቴ፥ 1992፥ "የክቡር ዶ/ር ሀዲስ ዓለማየሁ የሕይወት ታሪክና የስነጽሑፍ ስራዎቻቸው"፥ ገጽ 21።

[32] የዚች ጽሑፍ አቅራቢ በወጋቸው መሐል የሰማው።

[33] *ነጋሪት ጋዜጣ* (4ኛ ዓመት፥ ቁ. 8፥ 1937)።
[34] ዝኒ ከማሁ (7ኛ ዓመት፥ ቁ. 4፥ 1940)።
[35] ዝኒ ከማሁ (10ኛ ዓመት፥ ቁ. 9፥ 1943)።
[36] ዝኒ ከማሁ (12ኛ ዓመት፥ ቁ. 6፥ 1945)።
[37] ሐዲስ ዓለማየሁ፥ *የትምህርትና የተማሪ ቤት ትርጉም*፥ 1948፥ ገጽ 7።
[38] ከላይ የጠቀስነው መጽሐፍ ገጽ 111-12።
[39] ሐዲስ ዓለማየሁ፥ *የልምዣት*፥ 1980፥ ገጽ 5።
[40] *ነጋሪት ጋዜጣ*፥ (16ኛ ዓመት፥ ቁ. 8፥ 1945)።
[41] ዝኒ ከማሁ (19ኛ ዓመት፥ ቁ. 11፥ 1952)።
[42] አቢይ አበበ፥ *አውቀን እንታረም*፥ 1955፥ ገጽ 56
[43] ሐዲስ ዓለማየሁ፥ 1953 "ማስታወሻ"፥ ገጽ 1።
[44] በማስታወሻው በዚያው ገጽ ላይ ዝቅ ብሎ።
[45] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 3።
[46] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 13።
[47] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 13።
[48] *ነጋሪት ጋዜጣ* (20ኛ ዓመት፥ ቁ. 12፥ 1953)።
[49] ዝኒ ከማሁ (21ኛ ዓመት፥ ቁ. 2፥ 1954)።
[50] ሐዲስ ዓለማየሁ፥ *ኢትዮጵያ ምን ዐይነት አስተዳደር ያስፈልጋታል?*፥ 1965፥ ገጽ 4።
[51] ዳዊት አባተ፥ (ዓ.ም. የለውም) "ለኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት ኅብረሰባዊ ሥርዓት"። ጸሐፊው ስለሚደግፈው ሥርዐት ከማብራራት ይልቅ፥ ዶክተር ሐዲስና ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም በየበኩላቸው ለኢትዮጵያ ይበጃሉ ብለው ያቀረቧቸውን ሐሳቦች እማውገዝ ላይ ዐቅሙን ያባክናል።
[52] *ነጋሪት ጋዜጣ*፥ 25ኛ ዓመት፥ ቁ. 12፥ 1958)።
[53] ዝኒ ከማሁ፥ 28ኛ ዓመት፥ ቁ. 16፥ 1961)።
[54] የታሪክ ምሁርና ባለቅኔ የነበረው፥ ዶክተር ክነፈ ርግብ ዘለቀ ሻለቃ ሲሳይንና ናደው ዘካርያስን በዋቢነት በመጥቀስ ለዚች ጽሑፍ አቅራቢ በጨዋታ መሐል ያወጋው (1974?)።
[55] *አዲስ ዘመን*፥ ሐምሌ 16 ቀን፥ 1966።

[33] *ነጋሪት ጋዜጣ* (4ኛ ዓመት፥ ቁ. 8፥ 1937)።
[34] ዝኒ ከማሁ (7ኛ ዓመት፥ ቁ. 4፥ 1940)።
[35] ዝኒ ከማሁ (10ኛ ዓመት፥ ቁ.9፥ 1943)።
[36] ዝኒ ከማሁ (12ኛ ዓመት፥ ቁ. 6፥ 1945)።
[37] ሐዲስ ዓለማየሁ፥ *የትምህርትና የተማሪ ቤት ትርጉም*፥ 1948፥ ገጽ 7።
[38] ከላይ የጠቀስነው መጽሐፍ ገጽ 111-12።
[39] ሐዲስ ዓለማየሁ፥ *የልምዣት*፥ 1980፥ ገጽ 5።
[40] *ነጋሪት ጋዜጣ*፥ (16ኛ ዓመት፥ ቁ. 8፥ 1945)።
[41] ዝኒ ከማሁ (19ኛ ዓመት፥ ቁ. 11፥ 1952)።
[42] አቢይ አበበ፥ *አውቀን እንታረም*፥ 1955፥ ገጽ 56
[43] ሐዲስ ዓለማየሁ፥ 1953 "ማስታወሻ"፥ ገጽ 1።
[44] በማስታወሻው በዚያው ገጽ ላይ ዝቅ ብሎ።
[45] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 3።
[46] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 13።
[47] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 13።
[48] *ነጋሪት ጋዜጣ* (20ኛ ዓመት፥ ቁ. 12፥ 1953)።
[49] ዝኒ ከማሁ (21ኛ ዓመት፥ ቁ. 2፥ 1954)።
[50] ሐዲስ ዓለማየሁ፥ *ኢትዮጵያ ምን ዐይነት አስተዳደር ያስፈልጋታል?*፥ 1965፥ ገጽ 4።
[51] ዳዊት አባተ፥ (ዓ.ም. የለውም) "ለኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት ኅብረሰባዊ ሥርዓት"። ጸሐፊው ስለሚደግፈው ሥርዐት ከማብራራት ይልቅ፥ ዶክተር ሐዲስና ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም በየበኩላቸው ለኢትዮጵያ ይበጃሉ ብለው ያቀረቧቸውን ሐሳቦች እማውገዝ ላይ ዐቅሙን ያባክናል።
[52] *ነጋሪት ጋዜጣ*፥ 25ኛ ዓመት፥ ቁ. 12፥ 1958)።
[53] ዝኒ ከማሁ፥ 28ኛ ዓመት፥ ቁ. 16፥ 1961)።
[54] የታሪክ ምሁርና ባለቅኔ የነበረው፥ ዶክተር ክነፈ ርግብ ዘለቀ ሻለቃ ሲሳይንና ናደው ዘካርያስን በዋቢነት በመጥቀስ ለዚች ጽሑፍ አቅራቢ በጨዋታ መሐል ያወጋው (1974?)።
[55] *አዲስ ዘመን*፥ ሐምሌ 16 ቀን፥ 1966።